# ኢትዮጵያን በጭላንጭል

## (የወደፊቷ ኢትዮጵያን የፖለቲካ አስተዳደር ለመመስረት የአውሮፓውያን የፖለቲካ አስተዳደር ልምድ)

ኢሳት ባዘጋጀው የምስራቅ አፍሪካ ዝግጅት (ሜይ 9-10 2015) ላይ የቀረበ መጣጥፍ ነው።[1] ሆኖም ግን መጠነኛ መሻሻል ታክሎበታል።

በአየለ ታደሰ*

**አጭር መግቢያ**

የ1966 ዓ.ም. ሕዝባዊ እንቅስቃሴ የከሸፈው "የዲሞክራሲ ሽግግር" ስትራቴጂ አቅጣጫ ጉድለት፤ እንዲሁም "የጊዜያዊ ህዝባዊ መንግሥት" ጥያቄም ቢሆን የአጭርና የረጅም ጊዜ ጠቋሚ የፖለቲካ ዓላማና ንድፍ ስላልነበረው ነው። ስለዚህ አገራችን ኢትዮጵያ ካለፉት 40 ዓመታት ወዲህ ማርክሳውያን በነደፉት የምጣኔ ሃብትና የፖለቲካ ፍልስፍና በመመራት የተደናበረ አስተዳደራዊ መንገድ እየተከተለች ትገኛለች። ቀደም ባለው 20 ዓመታት በወታደራዊው አስተዳደር በመለጠቅም አሁን በ"አብዮታዊ ዲሞክራሲ" ስም የሚመራው ጎጠኛ ነፃ አውጪ የሕወሃት ፓርቲ አስተዳደር እየታመሰች ትገኛለች። በዚህ በሕወሃት ዘመን (ቢገባንም ባይገባንም) ተደጋግሞ የተነገረን አንድ ነገር አለ። ይኸውም "ኢትዮጵያዊው" የሆነ ሁሉ አይፈለግም። ኢትዮጵያዊ የሆነ ግለሰብ በገዛ ሃገሩ እንዳይካፈልም ሆነ እንዳይሳተፍ የተከለከለው በሁሉም መስክ ነው - በፖለቲካውና በምጣኔ ሀብት ዘርፍ፤ መሬት ኖሮት አርሶ እንዳይኖረው፤ ከተማም ሆነ ገጠር ውስጥ ስራ ሰርቶ እንዳይተዳደር፤ አገሩ ውስጥ በሰላም ኑሮውን እንዳይኖር፤ ትምህርት እንዳይማር ወዘተ መጠነ ሰፊ ዘመቻ እየተደረገበት ይገኛል።

ታዲያ አገራችን ኢትዮጵያ ውስጥ ወደድንም ጠላንም፤ በኃይልም ሆነ በአመፅ በቅርቡ ለውጥ መምጣቱ አይቀርም። የጊዜው ጥያቄ -"ዛሬ" ሕወሃት ከሥልጣን ቢወገድ ምን ዓይነት የአስተዳደር አማራጮች አሉ? የሚለውን ሃሳብ አንስቶ ተግባራዊ መንገዶቹን መፈተሹ አስፈላጊና ግዴታም ነው።

እንደሚታወቀው ለሆድ ውስጥ ተውሳክ መድኃኒቱ ኮሶ ነው። በተለይም በዚህ ዘመን ያለው ወጣቱ ትውልድ ማወቅ የሚገባው ከቻይና የተቀዳው የወያኔ "አብዮታዊ ዲሞክራሲ" የኢትዮጵያውያን ተውሳክ ሲሆን መድኃኒቱ ደግሞ ከዚህ "አብዮታዊ ዲሞክራሲ" ተውሳክ ለመውጣት ከምስራቅ አውሮፓውያን "ዲሞክራሲያዊ የፖለቲካ ሽግግር" ልምድ በመቅሰም ከራሳችን የፖለቲካ አስተደዳደር፤ ታሪክ፤ ልምድና ባህል ጋር ማዋሃድ ተገቢ ነው የሚል ሃሳብ አለኝ። ምክንያቱም በአንድ በኩል ይህ ዓይነቱ ሽግግር በተግባር የተፈተነ ስለሆነ፤ በሌላ በኩል ደግሞ የፖለቲካ ልምድ በአገራት መካከል ተወራራሽ ነው።

ይህች "ኢትዮጵያ በጭላንጭል" የምትለዋን አጭር መጣጥፍ የምታተኩረው የፖለቲካ አስተዳደር ምንጭና ዓይነቶችን በመጠኑ በመፈተሽ፤ ከአንድ ፓርቲ ጭቆና ወጥተው ወደ ዲሞክራሲ በአጭር ጊዜ ውስጥ የተሸጋገሩትን የበርካታ አገራትን ልምድ በማካፈል ተግባራዊ የአስተዳደር አማራጮችን ይዛ ቀርባለች። "ጭላንጭል" ማለት በጭለማ ቤት ውስጥ በቀዳዳ የሚታይ ብርሃን ማለት ነው - የተስፋ ብርሃን።

መልካም ምንባብ።

*የሰው ልጅ መንግሥታዊ "የአስተዳደር መዋቅር" ምንጭ*

በዘመናችን ስለ "ዘመናዊ አስተዳደር" ስንሰማ ብዙዎቻችን እንገረም ይሆናል። በተለያዩ አገራትም ሆነ በዓለም አቀፍ ደረጃ ያሉትን ትላልቅ ድርጅቶች "አስተዳደራዊ ስርዓታቸውን" እያየን እንዲሁም አገራት ውስጥ ከሰፈነው የዲሞክራሲ መዋቅር አንስቶ እስከ ትላልቅና አነስተኛ ድርጅቶች ድረስ "የአስተዳደር ስርዓታቸውን" እያየን በአግራሞት "ወቸ ጉድ!" የምንልም አንጠፋም። ግን ውስጡን ጠለቅ ብለን ስንመረምር አገራትም ሆነ ድርጅቶች ውስጥ ያለው የአስተዳደር ስርዓትና መዋቅር እጅግ በጣም ተመሳሳይ ነው።

ኢትዮጵያ ለዓለም ያበረከተቻቸው ብዙ ነገሮች አሉ። ከነዚህም ነገሮች አንዱና ከላይ በጥቅሉ ያነሳሁት የ"አስተዳደር ስርዓትና መዋቅር" ነው። ይህንን ለማስረዳት የመጽሐፍ ቅዱስ መረጃ ለማቅረብ ግድ ይላል። እንደሚታወቀው ሦስቱ የዓለም ትላልቅ ኃይማኖቶች ማለትም የይሁዳዊ፣ የክርስትና እና የእስላም ዋና የእምነት ምንጫቸው መጽሐፍ ቅዱስ መሆኑ እሙን ነው።

ታሪኩ እንደዚህ ነው። ሙሴ አንድ ግብጻዊ ይገድላል። "...ፈርዖንም ይህን ነገር በሰማ ጊዜ ሙሴን ሊገድለው ፈለገ። ሙሴ ግን ከፈርዖን ፊት ኮበለለ፣ በምድያምም ምድር ተቀመጠ"።[2] ምድያም እንደቆየ ኢትዮጵያዊ ሚስት ያገባል። ሙሴ ከሚስቱ ቤተሰብ ጋር የቀረበ ቤተሰባዊ ግንኙነት ነበረውና ያለበትን የአስተዳደር ችግር ከአማቹ ጋር ይወያዩ ነበር። ሙሴ ለአማቹ ሲያማክራቸው የእስራኤል ህዝብ ለአስተዳደር አስቸጋሪ መሆኑን ይገልፅላቸዋል። ሙሴ አስተዳዳሪ በመሆኑ ደግሞ ያለበትን የስራ ብዛትና ዓይነት ሲገልፅላቸው - የተጣሉ ባልና ሚስቶችን ከማስታረቅ ጀምሮ እስከ ከፍተኛ የአስተዳደር ስራዎችን እንደሚያጠቃልል ያስረዳቸዋል። አማቹ የሙሴን አሳብ አዳምጠው ለሙሴ እንዲህ ብለው መከሩት። "አሁን የገለፅካቸውን ስራዎች ሁሉ ብቻህን ልስራ ካልክ ስራው ሊከብድህና ሊያሳብድህ ይችላል። ስለሆነም የምታቀርባቸውና የምታምናቸው ሰዎች በዙሪያህ ሰብስበህ ሹመት ስጣቸው። ሹመት የሰጠሃቸው ሹማምንቶችህም እነሱም ሌላ የበታቾቻቸውን ይሹሙ። ሹመት የሰጠሃቸው ሰዎች ስራዎችን በአግባቡ እንዲሰሩ አድርግ። እነሱ ካልቻሉትና ከአቅማቸው በላይ የሆነውን አቤቱታ ብቻ ላንተ ያስተላልፉ። የሾሞችህ የበታቾች ደግሞ ሊፈቱት የማይችሉትንና ከአቅማቸው በላይ የሆነውን አቤቱታ ብቻ ለሹሞችህ ያስተላልፉ። እንደዚህ አድርገህ ደረጃ በደረጃ የስራህን ጫና ልትቀንስ ትችላለህ። በዚያ ላይም አንተን የሚተካህ ትውልድ ያስፈልጋልና ተተኪው ሰው የአስተዳደር ስርዓት እንዲቀስም ልምድ እንዲያካብት ታደርጋለህ። የአስተዳደር ስርዓቱም እንዲህ እያለ ለትውልድ ይተላለፋል።" ብለው መከሩት።[3]


ታዲያ ኢትዮጵያዊው አማቹ የሰጡት የ"አስተዳደር ስርዓት" ምክር ኢትዮጵያ ውስጥ በወቅቱ እየተሰራበት ነበር። በርግጥም አሁን ያለው ዓለም ምስራቅና ምዕራብ፣ ሰሜንና ደቡብ በመባል ገና ሳይከፋፈልና አገራት የተለያየ ስም ከማግኘታቸው አስቀድሞ ኢትዮጵያ ውስጥ እንደዚህ ባለ የአስተዳደር ስርዓትና መዋቅር እየተመራች ነበር። በነገራችን ላይ ምድያም - ኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኝ የአንድ ጥንታዊ አካባቢ ስም ነው።

*መንግሥት ማለት ምን ማለት ነው? መንግሥታዊ የአስተዳደር መዋቅርስ?*

መንግሥት[4] ማለት በፖለቲካ አገዛዝ ነፃ የሆነ፣ ህግ የሚያወጣና ተግባራዊ የሚያደርግ፣ ዳር ድንበር ያለው፣ ነዋሪ ህዝብ ያለው፣ የራሱ የሆነ ታሪክና ባህል ያለው፣ ስርዓት ነው ይላል። መንግሥታዊ "የአስተዳደር መዋቅር" ደግሞ ህዝባዊ አገልግሎቶችን የሚያቀርብበት፣ ግብር የሚሰበስብበት፣ ፀጥታና ጥበቃ የሚያከናውንበት፣ በአገሪቱ ውስጥ የሚኖረው ነዋሪ ኅብረተሰብ ለመኖር አስፈላጊ የሆኑትን ነገሮች ለምሳሌ የጤና፣ የትምህርት፣ የእርዳታ የፀጥታ ወዘተ አገልግሎቶችን የሚያሟላበት፣ ነዋሪው ሰርቶ መኖር እንዲችል ማንኛውም አገልግሎቶችን የሚያቀርብበት አስተዳደራዊ መንገድ ወይም መዋቅር ነው።

የመንግሥት[5] አስተዳደርና መዋቅር እንዲኖር ቢያንስ ቢያንስ የሚከተሉት መሟላት ይገባቸዋል - አገር፤ ህዝብ፤ ዳር ድንበር፤ ባህልና ሉዓላዊነት ወዘተ።

እንግዲህ ከላይ እንዳየነው በጥንት የሙሴ ዘመን ኢትዮጵያ ውስጥ መንግሥትና መንግሥታዊ የአስተዳደር መዋቅር ነበር። የዘመናዊው ዓለማችን የመንግሥታዊ አስተዳደር መዋቅር ምንጩና መሠረቱም ከዚህ በታች ያለው ኢትዮጵያ ውስጥ የነበረው መዋቅር ነው።




## የንጉሣዊ ሥርዓት የአስተዳደር አወቃቀር

ኢትዮጵያ ለዘመናት ትተዳደር የነበረው በንጉሣዊ የዘውድ ስርዓት ሲሆን የአስተዳደር ስርዓቱ መዋቅር በተዋረድ ወደታች የተዋቀረ ነው። ከንጉሠ ነገሥት በታች የአካባቢ ንጉሥ ወይም ሹም ከአካባቢው ንጉሥ ወይም ሹም በታች ደግሞ ሌሎች የተሾሙ ሰዎች ነበሩ። ስራቸውም እንደ ሹመታቸው ይለያያል። አንዱ ሹም በሌላኛው ሹም ስራ ውስጥ ጣልቃ አይገባም። ለምሳሌ ንጉሠ ነገሥቱ በአካባቢ ንጉሥ ወይም ሹም ስራ ጣልቃ አይገቡም። ነገር ግን በአካባቢው ንጉሥ (አለቃ) የተበደሉ ሰዎች ለንጉሠ ነገሥቱ አቤቱታ ማቅረብ ይችላሉ። ንጉሠ ነገሥቱም በቀረበው አቤቱታ ዙሪያ ጣልቃ በመግባት ችግሩን ይዳኛሉ። የአካባቢው ንጉሥ ወይም ሹም አንዱ ስራው ግብር ሰብስቦ ለንጉሠ ነገሥቱ የማስገባት ግዴታና እንዲሁም የአካባቢውን ኅብረተሰብ ከወሮበሎችና ከአውሬዎች የመከላከል ኃላፊነትም አለበት። በነገራችን ላይ አብዛኛውን ጊዜ የአካባቢ ንጉሥ ወይም ሹም ብዙ ጊዜ የሚመረጠው በአካባቢው ነዋሪ ነው።

## ኢትዮጵያ በተሳከረ የአስተዳደር መንገድ

በመሰረቱ አገራችንን ኢትዮጵያ የጎዳት ሁለቱ የጀርመን ፈላስፎች ፍልስፍና ተግባራዊ ለማድረግ በሚደረገው ትንቅንቅ የተሳከረ መንገድ መከተል ስትጀምር ነው። ለዚህም ባለፉት 40 ዓመታት የደረሱትን ጉዳቶች ወደ ኋላ መቃኘት አስፈላጊ ነው። እነዚህ ሁለቱ የጀርመን "የተከበሩ" ፈላስፋዎች ግን ፍልስፍናቸው ለኢትዮጵያ ጠንቅና ማነቆ የሆኑት - ካርል ማርክስና ማርቲን ሉተር ይባላሉ። የካርል ማርክስ እንዲሁም ኤንግልስና ሌኒን ጥናት ያተኮረው የሰው ልጅ እድገት በአምስቱ ማኅበረሰብ ስርዓት ላይ ማለትም ከጋርዮሽ እስከ ኮሚኒስት የአስተዳደር ስርዓትና እንዲሁም የምጣኔ ሃብት እድገትን ያካተተ ነው። ጀርመናዊው ማርቲን ሉተር ደግሞ የሚታወቀው በፕሮቴስታንት እምነት ዙሪያ ባቀረበው የፍልስፍና እምነት ነው። ማለትም ፍልስፍናንና ኃይማኖትን በመቀየጥ፤ ቅድመ አዲስ ኪዳን እንዲሁም በ1ኛውና 2ኛው ክ/ዘ የተነሱትን ፍልስፍና ላይ የተመረኮዘ አዲስ የእምነት "እንቅስቃሴ" በአውሮፓ ፈጠረ። በነገራችን ላይ ፍልስፍናን የተመረኮዘ ኃይማኖት እና ኃይማኖትን የተመረኮዘ ፍልስፍና ሁለቱ ለየቅል ናቸው። ጀርመናዊው ማርቲን ሉተር የመሰረተው በፍልስፍና ላይ የተመረኮዘ ኃይማኖት ነው[6]። ይህ

መጣጥፍ የሚያተኩረው ከላይ እንደጠቀስኩት በካርል ማርክስ የሶሻሊዝም ምጣኔ ሃብትና አስተዳደራዊ ፖለቲካ ፍልስፍና ዙሪያ ይሆናል።

በጀርመኑ ካርል ማርክስ የተፃፈውና በሶቭየት ህብረቱ ሌኒን በተግባር በተረጎመው የሶሻሊስት ፖለቲካ ፍልስፍና ሳቢያ አገራችን ላይ በ"አብዮታዊ ዲሞክራሲና ሶሻሊዝም" ስርዓት ስም የተመሰረተው የፖለቲካ ስርዓት ከፍተኛ ደረጃ ላይ ደርሶ የአብዮታዊ ዲሞክራሲ አስተዳደር የኅብረተሰቡን አፍ አስዘግቶ፣ እንዲሁም ህዝቡ መሰረታዊ ህይወቱ ማለትም በምግብና በኑሮው መጣበት። ወኔውን አኮላሸ፣ ተሽቆጥቋጭና ፈሪ የሆነ ትውልድ እንዲያፈራ በመደረግ ላይ ነው። በሶሻሊስት ስርዓት "የራስን እድል በራስ የመወሰን እስከመገንጠል" በሚል ስም አገር አፍራሽ ነፃ አውጪ ድርጅቶች ተፈለፈሉ። ነፃ አውጪ ድርጅቶችም አገርና ወገን ገዳይ አስተዳደራዊ መዋቅር ዘረጉ። አገራችን ለልጆቿ ገዓነመ እሳት ሆነች፣ ለጠላቶቿም በቀላሉ ተንበርካኪ እንድትሆን መንገዱ ዘረጉላት። በመሰረቱ <u>የነፃ አውጪ ድርጅቶች ፍልስፍና አስተዳደራዊ መዋቅር በዚህ ዘመን የኋላ ቀርነት ምልክት ነው።</u> ምክንያቱም ከአገራት ልምድ እንደታየው የነፃ አውጪ ድርጅቶች በትረ ሥልጣኑን ከተቆጣጠሩ በኋላ ፍፁማዊ አገዛዝ እንጂ የህዝቡን ነፃነት ስለማያጎናፅፉ ነው። በዚህ ዘመን ደግሞ የህዝብን ድምፅ ማፈን፣ ነፃነቱን መንፈግ የማይቻልበት ወቅት ነው። እንዲሁም ዓለም ወደ አንድ አለም አቀፋዊ ጎዳና እያመራች ያለችበት ወቅት በመሆኑም ጭምር ነው - የነፃ አውጪ ድርጅቶች ፍልስፍናና አስተዳደራዊ መዋቅር የኋላ ቀርነት ምልክት ነው የሚባለው።

### የመንግሥት "አስተዳደር" ኃላፊነትና ግዴታ።

መንግሥትና የአስተዳደር መዋቅር የተለያዩ ሆነው ሊታዩ ይችላሉ። ዲሞክራሲ ባለባቸው አገራት መንግሥትና የአስተዳደር መዋቅር መጠነኛ የሆነ ልዩነት ይታይባቸዋል።
ለመሆኑ የአንድ አገር መንግሰታዊ አስተዳደር ኃላፊነትና ግዴታ[7] ምንና ምንን ያካትታል? የዘመናዊ አስተዳደር ጥራትንና ብስለትን ሚዛን ላይ አስቀምጦ ለመመዘን እንዲያመች ጥቂቶቹን የጋራ የሆኑ መመዘኛ ነጥቦች ልጥቀስ፣

1) የምጣኔ ሃብት፣ የፖለቲካና የአስተዳደር ወዘተ ህግ መቅረፅና ኅብረተሰቡን በወጣው ህግ መሠረት ሁሉንም ዜጋ በእኩል ዓይን ማስተዳደር፣
2) የኅብረተሰቡንም ሆነ የግብር ከፋዩን ኑሮ ከሚያውክ ጠላት ወይም ሰላም ከሚነሳ ኃይል መከላከል፣
3) የሚያስተዳድረውን አገር ዳር ድንበርና ብሎም ሉኣላዊነት ማስከበር፣
4) የአገሪቷን ቅርስም ሆነ ባህል ከትውልድ ወደ ትውልድ መተላለፉን ማረጋገጥ፣
5) የአገሪቷን የአጭርና ረጅም ጥቅም ማስጠበቅ፣
6) የኅብረተሰቡን የዕለት ተዕለት ኑሮ ለሚያውኩ ችግሮች መፍትሔ ማቅረብ፣
7) የዜጎችን መብት መጠበቅና የዜጎችን አቤቱታን ተቀብሎ መፍትሔ ማቅረብ፣
8) የምጣኔ ሃብት አገሪቱን በመጥቀም ላይ ያተኮረ እንጂ ለአስተዳደሩ በሚበጀው መልክ ለዘረፋ ፖሊሲ አለመሆኑን ማረጋገጥ፣ የገንዘብ እትመት ፖሊሲ፣ የሰራተኞች ፖሊሲ፣ ግብር መሰብሰብ፣ ዘላቂ የምጣኔ ሃብት መዋቅር መዘርጋት ወዘተ።
9) የትምህርትና የጤና ፖሊሲዎችን ለዜጎች በሚጠቅም መልኩ መዘርጋት፣
10) ከውጪ አገራቶች ጋር ግንኙነቶችን አገሪቱን በሚጠቅም መልክ ፖሊሲ መንደፍ፣ ዓለም አቀፋዊ ውክልናዎችን ሆነ ፕሮቶኮሎችንም ማክበር፣ ወዘተ

የመንግስታዊ አስተዳደር ኃላፊነትና ግዴታው እስከምን ደረጃ ድረስ መሄድ እንዳለበት ለማነፃፀር እንዲያመቹን በዓለም አቀፍ ደረጃና በኢትዮጵያ ደረጃ በማለት ያሉትን የአስተዳደር ዓይነት ከታች በሰንጠረዥ እንመለከታለን። ኢትዮጵያ አገራችን ውስጥም በሦስቱም አስተዳደሮች የነበረውን ባህሪይ ለማሳየት (የአስተዳደሩ መሪዎችም ሆነ አስተዳደሩ <u>ኃላፊነት ይሰማዋል ወይም ኃላፊነት አይሰማውም</u>።) በሚሉ ነጥቦች ነጥዬ ላወዳድር።

በዓለም አቀፍ ደረጃ በምሳሌነት የተወሰዱት አገራት

1) ዘመናዊ የዘውድ አስተዳር ያለባቸው አገራት - ለምሳሌ እንግሊዝ፣ ስዊድን፣ ጃፓን
2) ዲሞክራሲያዊ አስተዳደር ያለባቸው አገራት - ለምሳሌ ጀርመን፣ ፈረንሳይ፣ ሃንጋሪ፣ አሜሪካ
3) ፍፁማዊ አስተዳደር ያለባቸው አገራት - ለምሳሌ ራሺያ፣ ቻይና፣ ኤርትራ፣ ሰሜን ኮሪያ፣

በኢትዮጵያ ደረጃ ደግሞ ሦስት አስተዳደሮችን እናያለን።

1) የኃይለ ሥላሴ የዘውድ አስተዳደር፣
2) የደርግ ወታደራዊ አስተዳደርና
3) አሁን በሥልጣን ላይ ያለውን የሕወሃት ኀሳዊ አስተዳደርን እንመለከታለን።

| | የአስተዳደር ዓይነት | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | በዓለም አቀፍ ደረጃ | | | በኢትዮጵያ ደረጃ | | |
| የኃላፊነት ሥራዎች | ዘመናዊ የዘውድ አስተዳደር | ደሞክራሲያዊ አስተዳደር | ፍፁማዊ አስተዳደር | የኃይለ ሥላሴ የዘውድ አስተዳደር | የደርግ ወታደራዊ አስተዳደር | የሕወሃት ፍፁማዊ አስተዳደር |
| | ኃላፊነት | | | ኃላፊነት | | |
| ህግና ደንብን መቅረፅ | ይሰማዋል | ይሰማዋል | ይሰማዋል | ይሰማዋል | ይሰማዋል | ይሰማዋል |
| በህግ መተዳደር / ማስተዳደር | ይሰማዋል | ይሰማዋል | አይሰማውም | ይሰማዋል | አይሰማውም | አይሰማውም |
| ሕዝብና አገሩን ከጠላት መከላከል | ይሰማዋል | ይሰማዋል | ይሰማዋል | ይሰማዋል | ይሰማዋል | አይሰማውም |
| ሉአላዊነትን ማስከበር | ይሰማዋል | ይሰማዋል | ይሰማዋል | ይሰማዋል | ይሰማዋል | አይሰማውም |
| የአገሪቷን ቅርስም ሆነ ባህል ማስጠበቅ | ይሰማዋል | ይሰማዋል | ይሰማዋል | ይሰማዋል | ይሰማዋል | አይሰማውም |
| አገርን ከትውልድ ወደ ትውልድ ማስተላለፍ | ይሰማዋል | ይሰማዋል | ይሰማዋል | ይሰማዋል | ይሰማዋል | አይሰማውም |
| ለሚፈጠሩ ማኅበራዊ ችግሮች መፍትሔ ማቅረብ | ይሰማዋል | ይሰማዋል | አይሰማውም | ይሰማዋል | አይሰማውም | አይሰማውም |
| የአገሪቷን ጥቅም ማስጠበቅ | ይሰማዋል | ይሰማዋል | ይሰማዋል | ይሰማዋል | ይሰማዋል | አይሰማውም |
| ሁሉንም ዜጋ በእኩል ዓይን ማስተዳደር | ይሰማዋል | ይሰማዋል | አይሰማውም | ይሰማዋል | አይሰማውም | አይሰማውም |
| የሁሉንም ዜጋ መብት ማክበር | ይሰማዋል | ይሰማዋል | አይሰማውም | አይሰማውም | አይሰማውም | አይሰማውም |
| ከውጪ አገራቶች ጋር ያለው ግንኙነቶች ፖሊሲ | ይሰማዋል | ይሰማዋል | አይሰማውም | ይሰማዋል | ይሰማዋል | አይሰማውም |
| የትምህርትና የጤና ፖሊሲ | ይሰማዋል | ይሰማዋል | አይሰማውም | ይሰማዋል | ይሰማዋል | አይሰማውም |
| በምጣኔ ሃብት ፖሊሲ ንብረት ለራሱ ማካበት | ይሰማዋል | ይሰማዋል | አይሰማውም | ይሰማዋል | ይሰማዋል | አይሰማውም |
| አገራዊ ፍቅርና አገራዊ ስሜት | ይሰማዋል | ይሰማዋል | ይሰማዋል | ይሰማዋል | ይሰማዋል | አይሰማውም |
| አስተዳደሩ የሚሰማው የኃላፊነት ሥራዎች | 14 | 14 | 7 | 13 | 10 | 1 |
| የኃላፊነት ሥራዎች በመቶ (%) ሲለካ | 100% | 100% | 50% | 93% | 71% | 7% |

እንግዲህ በሰንጠረዡ ላይ እንዳሳየሁት መንግሥታዊ ሥራዎች ውጤቱን ደግሞ በጥቅሉ እንመልከት።

<u>በዓለም አቀፍ ደረጃ፣</u>

1) የዘመናዊ ዘውድና የዲሞክራሲያዊ አስተዳደር ባለባቸው አገራት የአስተዳደሩ መሪዎች የተጣለባቸውን ኃላፊነት በተመሳሳይነት ሲወጡ እናያለን። የአስተዳደሩ መሪዎች ለሚወጡት ህጎች ተገዢዎች ናቸው። ለግለሰቦች መብት ይቆረቆራሉ። ለማኅበራዊ ችግሮች መፍትሔ የሚቀርበው በውይይትና በምርጫ ነው። ለአገራቸው ቅርስና ባህል ከፍተኛ አክብሮት አላቸው። የአስተዳደሩ መሪዎቹ አገራዊ ፍቅርና ስሜት አላቸው። <u>የአገራቸውን ዳር ድንበር አስጠብቀው ለትውልድ ያስተላልፋሉ</u>። የዘመናዊ ዘውድና የዲሞክራሲያዊ አስተዳደር ባለባቸው አገራት የአስተዳደሩ መሪዎች የኃላፊነት ሥራዎች ለመወጣት ሙሉ በሙሉ ኃላፊነትና ግዴታ ይሰማቸዋል።
2) ፍጹማዊ አስተዳደር ባለባቸው አገራት ውስጥ ደግሞ የአስተዳደሩ መሪዎች ራሳቸው ያወጡትን ህግ እንኳን አያከብሩም። ለግለሰቦች መብት አይቆረቆሩም። የማኅበራዊ ችግሮች መፍትሔ የሚፈቱት በጠመንጃ አፈሙዝ ነው። ከማኅበራዊ ፖሊሲዎች ይልቅ ወታደራዊና የስለላ መረቦች ቅድሚያ ይሰጣሉ። በተቃራኒው የአስተዳደሩ መሪዎቹ አገራዊ ፍቅርና ስሜት አላቸው። <u>የአገሪቷን ዳር ድንበር አስጠብቀው ለትውልድ ያስተላልፋሉ</u>። <u>ፍጹማዊ አስተዳደር ባለባቸው የዓለም አገራት አስተዳደር መሪዎች ከላይ ከቀረቡት 14 መስፈርቶች ውስጥ በ7ቶቹ ወይም 50% ኃላፊነትና ግዴታ ይሰማቸዋል።</u>

<u>በኢትዮጵያ ደረጃ፣</u>

1) የኃይለ ሥላሴ የዘውድ አስተዳደር ወቅታዊው የዓለም አቀፍ ሁኔታ እንደፈቀደላቸው የተጣለባቸውን የኃላፊነት ሥራዎች ለመወጣት ሙሉ ኃላፊነትና ግዴታ ይሰማቸዋል። እንደ ምሳሌ የማነሳው ገና

አፍሪካ በአውሮፓውያን ቅኝ ግዛት ተይዛ በነበረበት ወቅት የኃይለ ሥላሴ አስተዳደር በ1923 ዓ.ም. ህገ-መንግስት[8] በማርቀቅ አቅርበው ነበር። ግን የሁሉም ዜጋ መብት በእኩል አይከበርም ነበር። ለምሳሌ የጭሰኛው መብት (ከባላባት መብት አንፃር ሲታይ) ሙሉ በሙሉ አይከበርለትም። በማኅበረሰቡ ውስጥ የሚፈጠሩትን ችግሮች በባህላዊ የሰላምና የሽምግልና መንገድ ለማቃለል የአስተዳደሩ መሪዎች ኃላፊነት ይሰማቸዋል። መሪዎቹ ከፍተኛ አገራዊ ፍቅርና ስሜት አላቸው። የአገርን ዳር ድንበር አስጠብቆ ለትውልድ የማስተላለፍ ኃላፊነትና ግዴታ ይሰማቸዋል። ከዓለም አቀፍ ዘውዳዊ አስተዳደር አንፃር ሲታይ የኃይለ ሥላሴ የዘውድ አስተዳደር ከላይ ከቀረቡት 14 መስፈርቶች ውስጥ በ13ቶቹ ወይም 93% ኃላፊነትና ግዴታ ይሰማቸዋል።

2) የደርግ ወታደራዊ አስተዳደር አምባገነናዊ አስተዳደር ነበር። የ"ማርክሳዊ ሌኒናዊ"ን ፍልስፍና መንገድ የሚቃወም ዜጋ የሚጠብቀው የ"አብዮት ሰይፍ - የፍየል ወጠጤ" ነው። ለማኅበራዊ ችግሮች መፍትሔ የሚፈቱት በጠመንጃ አፈሙዝ ነው። የአስተዳደሩ መሪዎች አገራዊ ፍቅርና ስሜት አላቸው። የአገርን ዳር ድንበር አስጠብቆ ለትውልድ ያስተላልፋሉ። የደርግ አስተዳደር ከዓለም አቀፍ ፍጹማዊ አስተዳደር ካለባቸው አገራት አንፃር ሲታይና ከላይ ከቀረቡት 14 መስፈርቶች ውስጥ በ10ሩ መስፈርቶች ወይም 71% ኃላፊነትና ግዴታ አስተዳደሩ ይሰማዋል።
3) የሕወሃት አስተዳደር ፍፁም አምባገነናዊ አስተዳደር ነው። የሕወሃት አስተዳዳሪ መሪዎች ከሌሎቹ የዓለምና ካለፉት የኢትዮጵያ አስተዳደራት ጋር የሚመሳሰላቸው በአንድ ነገር ብቻ ሲሆን ይኸውም ህግና ደንብን በመቅረፅ ነው። የሕወሃት አስተዳደር በተለይም መምታት የሚፈልገው ግለሰብ/ቡድን ካለ ህግና ደንብን ለመቅረፅ እጅግ ፈጣን ነው። ለምሳሌ አንድ በጉቦ ያሰሩት ባለስልጣን መልሶ እስር ቤት ለመክተት አዲስ ህግ እንደረቀቀና ወይም የግል ጋዜጠኞችን ለማጥፋት የፀረ አሸባሪ ህጉ እንዴት እንደረቀቀና እንደፀደቀ መገንዘቡ በቂ ነው።

ከዓለም አቀፍም ሆነ በኢትዮጵያ ውስጥ ከነበሩት አስተዳደሮች የሚለዩበት ደግሞ፤

ሀ) የአስተዳደሩ መሪዎች የኢትዮጵያ ዳር ድንበር አስጠብቆ ወይም ሉአላዊነቷን አስከብሮ ለትውልድ የማስተላለፍ ኃላፊነትና ግዴታ እንዳለባቸው አይሰማቸውም።

ለ) የሕወሃት አስተዳደር መሪዎች የተለየ የምጣኔ ሃብት ፖሊሲ በመዘርጋት የአገሪቱን ንብረት ለጦር አዛዦችና ለጥቂቶቹ ባለስልጣናት የተትረፈረፈ ሃብት አጋብሰዋል፤ እያግበሰበሱም ይገኛሉ። ከዚህም በተጨማሪ የአገሪቱ ዜጎችም እንዳይግባቡና አብረው እንዳይኖሩ ብሔራዊ ቋንቋንና ባህላዊ ቅርሶችን በማጥፋት፤ ዜጎችን "በልማት ስም" የተወለዱበትን ያደጉበትንና ቀዬና ቤታቸውን በእሳት በማቃጠል ለስደት እንዲዳረጉ በማድረግ ህወሃት በፖሊሲ እየተመራ መሆኑ የአደባባይ ሚስጥር ነው።

ሐ) የሕወሃት አስተዳደር መሪዎቹ ግላዊ ፍቅር እንጂ አገራዊ ፍቅርና ስሜት የላቸውም።

መ) የሕወሃት አስተዳደር መሪዎች የሚያስተዳድሩትን አገር እንኳ የረጅም ጊዜ ጥቅም የማስጠበቅ ኃላፊነት አይሰማቸውም። እንደ ምሳሌ የማነሳው፤ የአገሪቱን መሬት ሸንሽኖ ለባለስልጣኖች መስጠትና ለውጪ ድርጅቶች በኮንትራት ወይም ውል ስም መስጠት፤ ቅጥ ያጣ የውጭ አገር ገንዘብ ብድር ፖሊሲ፤ የመሬት ሊዝ ፖሊሲ (በየትኛውም አገር ያልተገበረ ፖሊሲ ነው።)፤ የአባይ ወንዝ ፖሊሲ፤ የትምህርት ፖሊሲ ትውልድን ለመግደያነት ጥቅም ላይ ማዋሉ፤ የተማሩ ኃይል፤ በአስተሳሰቡ ነጻ የሆነ ግለሰቦችን በማሳደድ፤ ሞራላቸውን በማላሸቅ ላይ ይገኛል።

መ) የሕወሃት አስተዳደር በሚያስተዳድረው ህዝብ ላይ ጠላት ቢመጣበት ወይም ህዝቡ በጠላት ቢጠቃ ወታደር በመላክ ህዝቡን ለመከላከል ፍላጎትም ሆነ ችሎታ የለውም። በቅርቡ በሱዳን በኩል በነዋሪው ህዝቡ ላይ ጥቃት ሲመጣበት ሕወሃት ሊደርስለት አለመቻሉ ያስታውሷል። እንዲሁም ኢትዮጵያውያኖች በሳዑዲ ዓረቢያና በደቡብ አፍሪካ ሲገደሉ የህወሃት አስተዳደር መሪዎች እንደ መንግስታዊ መዋቅር እንኳ አልተንቀሳቀሰም።


ስለሆነም የሕወሃት አስተዳደር በዓለም ውስጥ ፍጹማዊ አስተዳደር ካለባቸው አገራትም ሆነ ኢትዮጵያ ውስጥ ከነበሩት ዘውዳዊና ደርግ አስተዳደር አንፃር ሲታይ ከላይ ከቀረቡት 14

መስፈርቶች ውስጥ በ1ዱ ብቻ ወይም 7% (ሰባት በመቶ) ብቻ የመንግሥታዊ አስተዳደር ኃላፊነትና ግዴታ እንዳለበት ይሰማዋል።

ይህ የሕወሃት የአስተዳደር ፀባዩ ከሌሎቹ የዓለምና ኢትዮጵያ ውስጥ ለዘመናት ከነበሩት የአስተዳደር ዓይነቶች የተለየ ያደርገዋል። የሕወሃት አስተዳደር የኀሳዊ፣ የፋሽዝምና የማፍያ[9] ፀባያትን አቀናብሮ በመያዙ ልዩ "የአስተዳደር መዋቅር" ፈጥሯል። እንዲህ ያለ የአስተዳደር መዋቅርና አደረጃጀት ከዚህ በፊት በዓለምም ሆነ በኢትዮጵያ ተሰምቶ አይታወቅም። ስለሆነም በመንግሥታዊ የአስተዳደር ጥናት ውስጥ የሕወሃት አስተዳደር ፋሽዝምና ማፍያ ልዩ መገለጫው ሆኖ ወደፊት በኢትዮጵያም ሆነ በዓለም ታሪክ በእኩይ አስተዳደርዊ መዋቅር ሊዘከር የሚገባው ይመስለኛል።

## የሕወሃት የአስተዳደር መዋቅር

በአሁኑ ወቅት ያለው የሕወሃት አስተዳደር መዋቅር ምን ይመስላል? ሕወሃት እንደ ፖለቲካ ፓርቲ፣ የሕወሃት መሪዎችና የሕወሃት አስተዳደር ሁሉም አንድ ናቸው። ምንም ልዩነት የላቸውም። የፓርቲው መሪዎች ተወያይተው የሚወስኗቸው ውሳኔዎች በአስተዳደሩ መዋቅር ስር በተግባር ይገለፃል። ሁሉም የአስተዳደሩ ተቋማት በአንድ ሳንባ ስለሚተነፍሱ አስተዳደሩ ውሳኔውን ተግባራዊ ያደርገዋል። ስለሆነም ሕወሃት (የነፃ አውጪ ድርጅት እንደመሆኑ መጠን) የአስተዳደር መዋቅሩን ከታች እንመልከት።




ሕወሃት የምጣኔ ሃብቱን እንደተቆጣጠረ እናያለን። በተለይም የሕወሃት መሪዎችና የጦር አዛገሮች የአገሪቱን ምጣኔ ሃብት ሙሉ በሙሉ መያዛቸውን እንመለከታለን።

### የፓርቲዎች እንደ አሸን መፍላት

አገራችን ኢትዮጵያ በለውጥ ዋዜማ ውስጥ ትገኛለች። ታዲያ አሁን ባለችበት የለውጥ ዋዜማ፣ ጊዜና ሁኔታ እንደ አሸን የፈሉ ብቻ ሳይሆኑ አስተሳሰባቸውና አመለካከታቸው የጠበበና የማይገጥም 100 የሚደርሱ የፖለቲካ ፓርቲዎች ያለወቅቱ የፈሉባት አገር ሆናለች። ተለጣፊና ተቃዋሚ ፓርቲዎች። በርግጥ አብዛኛው "ተለጣፊ" የፖለቲካ ፓርቲዎች የተፈለፈሉት በሕወሃት አስተዳደር ነው። እነዚህ "ተለጣፊ" የፖለቲካ ፓርቲዎች አንድ ቋንቋ እንዳይናገሩ፣ እንዳይስማሙና እንዳይግባቡ ተደርገው

የተዋቀሩ ናቸው። ከዚህም በተጨማሪ የአገራቸው ሁኔታ ያሳሰባቸው ግለሰቦችም "ተቃዋሚ" ፓርቲዎችም በሰላማዊ መንገድ ለመታገል ብዙ መስዋዕት ከፍለዋል። ለእስርና ለስደትም ተዳርገዋል። ሆኖም ግን በአገራችን ውስጥ ዓይነታቸው የበዛ የፖለቲካ ፓርቲዎች እንደ አሸን መፍላት በራሱ ከፈረሱ ፊት ጋሪውን እንደማስቀደም ሆኖ ሊታይ ይችላል። ፈረሱ ነው ጋሪውን የሚጎትተው እንጂ በተገላቢጦሽ ጋሪው ፈረሱን ሊጎትት አይችልም። የፈረሱ ከጋሪው በፊት የመሆኑ ሁኔታ መቅደም ይኖርበታል። አብዛኛው ህዝብ ለእውነተኞቹና ተቃዋሚ ለነበሩት በሰላማዊ ለሚታገሉት የፖለቲካ ፓርቲዎችም የ"ተባበሩ ወይም ተሰባበሩ" ጥሪ የሚያቀርበው ይህንን የፖለቲካ ድርጅቶች ብዛትና ውጥንቅጥ ማየት ስለታከተው ነው።

በአንፃሩ ደግሞ የ"ተባበሩ ወይም ተሰባበሩ" ጥያቄ ማንሳቱ ተገቢ ቢሆንም ተግባራዊ ሊሆን የሚችልበት የተመቻቸ ሁኔታ አልተፈጠረም። በሰላም የሚታገሉት ተቃዋሚ ፖለቲካ ፓርቲዎች በተለያዩ ምክንያቶች "ጥምረት"ና "ውህደት" መፍጠር አልቻሉም። በሌላ በኩል ደግሞ ነፃ የሆነ የምርጫ ቦርድ፣ ነፃ የመወያያና የመሰባሰቢያ መድረክ፣ ወዘተ በሌለበት ሁኔታ ምርጫ ማድረግ ጊዜ፣ ገንዘብና ጉልበት ከማባከን በቀር ምንም ትርጉም የለውም። ታዲያ ምን ዓይነት ሁኔታ መፈጠር አለበት? ከአምባገነናዊ ስርዓት ወደ ዲሞክራሲ ጎዳና እንዴት በአጭር ጊዜ ውስጥና በተቀላጠፈ መንገድ መግባት ይቻላል? ለሚለው ጥያቄ የምስራቅ አውሮፓ አገራት ከአምባገነን ስርዓት እንዴት እንደወጡ የፖለቲካ ልምዳቸውን ማየቱ እጅግ በጣም ጠቃሚ ነው።


አንድ ነገር ልጨምር የጦር መሳሪያ ይዘው ሕወሃትን የሚታገሉት የተለያዩ የጦር ተዋጊ ድርጅቶች "ጥምረት"ና "ውህደት" እየፈጠሩ ይገኛሉ። ይህ በነፕሮፌሰር ብርሃኑ ነጋና ራስ አንዳርጋቸው ፅጌ ("ራስ" የሚለው ስያሜ ያገኙት ኦክቶበር 2013 አትላንታ ነዋሪ በሆኑ ኢትዮጵያውያኖች ነው።) በመሰረቱት ግንቦት 7 ድርጅት ሲሆን በድርጅቱ በኩል እየተደረገ ያለው የ"ጥምረት"ና "ውህደት" እንቅስቃሴ በተለይም በጦር የተደራጁ ኃይሎች ጥምረትና ውህደት በዓለምም ሆነ በአገራችን ተሰምቶ የማይታወቅ ነገር ግን የዘመናችን አዲስና ትልቅ እመርታ ነው። ምክንያቱም ከተለያዩ አገራት ታሪክ እንደምንማረው በጦር የተደራጁ ተዋጊ ኃይሎች እርስ በርስ ሲናቆሩ እንጂ ተስማምተውና ተዋህደው አንድ ሆነው ጥምረት ሲፈጥሩ አይታይምና። ምናልባት ይህ ዓይነቱ ውህደት ተሳክቶ ወደ ዲሞክራሲ ጎዳና ከወሰደን በ"አስተዳደራዊ ስርዓት መስክ" በኩል ሌላ አዲስና አስተማሪ የታሪክ ምዕራፍ ይከፈታል የሚል እምነት አለኝ።

## የምስራቅ አውሮፓውያን ከአምባገነን ወደ ዲሞክራሲ የለውጥ ጉዞ

የመጀመሪያዋ የምስራቅ አውሮፓ የዲሞክራሲ ሽግግር ለውጥ ያካሄደችው ፖላንድ ነበረች። ታዲያ የፖላንድ የዲሞክራሲ ለውጥ አንዳንድ የአሰራር ግድፈቶች ስለነበሩበት ወደ 29 የሚደርሱ የፖለቲካ ፓርቲዎች በአንድ ጊዜ ምርጫ ወደ ፓርላማ ሊገቡ ቻሉ። ከነዚህም አንዱ ወደ ፓርላማ ለመግባት የፖለቲካ ፓርቲ የሆኑት እጩዎች በአገር አቀፍ ደረጃ ምርጫ ላይ መወዳደር አይጠበቅባቸውም ነበር። ማለትም ለእያንዳንዱ አካባቢ የተወሰኑ የፓርላማ መቀመጫዎች ተወስኖ ነበርና ፓርቲዎች አንድ አካባቢ ማለትም ወረዳ ወይም አውራጃ ላይ በአነስተኛ ድምፅ ቢያሸንፉ እንኳ ወደ ፓርላማ ሊያስገባቸው የሚያስችል ሁኔታዎች ነበሩ።

ሃንጋሪያውያን ከፖላንድ የምርጫ ልምድ በመማር ነገር ግን የተሻለ የምርጫ መንገድ በመቀየስ ወደ ፓርላማ ያስገቡት ስድስት የፖለቲካ ፓርቲዎች ብቻ ነበሩ። ሌሎች የምስራቅ አውሮፓ አገራትም ይህንን የሃንጋሪያውያን የዲሞክራሲ ሽግግር የለውጥ መስመር ስለተከተሉ ስለ ሃንጋሪ የፖለቲካ ለውጥ በመጠኑ ልጥቀስ።

## የምሥራቅ አውሮፓውያን የአስተዳደር መዋቅር ከ1989 እ. አ. አ. በፊት




### ለመሆኑ በሃንጋሪ የተደረገው የለውጥ ሂደት[10] ምን ይመስል ነበር?

ወቅቱ 1989 ዓ.ም. ሲሆን

1) ካዳር ያኖሽ የሃንጋሪ ኮሚኒስት መሪ ሆኖ የአገሪቱ መንበረ ስልጣኑን በመያዝ ይመራ ነበር።
2) ሃንጋሪ 21.2 ቢሊዮን የአሜሪካን ዶላር[11] ዕዳ ውስጥ ተነክራ ነበር። (አሁን ኢትዮጵያ አገራችን 30 ቢሊየን ዶላር[12] በውጪ አገራት ዕዳ እንደተነከረችው ማለት ነው።)
3) ከዚህም በተጨማሪ በ1980ዎቹ መጨረሻ አካባቢ የሶቪየት ህብረት መሪ የነበረው ሚካኤል ጎርባቾቭ በትረ ስልጣኑን ከጨበጠ በኋላ የምስራቅ አውሮፓ አገራት የአስተዳደር ለውጥ እንዲያመጡ ግፊት ያደረገበት ወቅት ነበር።
4) ሃንጋሪ ውስጥ 13 የሚደርሱ አነስተኛ የማኅበረሰብ ዘውጌዎች አሉ[13]።

እና በፕሬዝዳንቱ ካዳር ያኖሽ "መልካም ፈቃድ" የሶሻሊስት ፓርቲው የሚመራው ፓርላሜንት አንድ ጥቅል በውሳኔ መልክ አሳለፈ። ስሙም የዲሞክራሲ ጥቅል "democracy package" ተብሎ ይጠራል። ይህ የዲሞክራሲ ጥቅል የሚያጠቃልለው በአገሪቱ የሚገኙት የሙያ ማህበራቶች፣ በነፃ መሰብሰብና መንቀሳቀስ፣ ነፃ የጋዜጣ እትመት፣ አዲስ የምርጫ ህግ፣ እና የአገሪቱ ህገ መንግሥት እንዲሻሻልና መሠረታዊ ለውጥ እንዲደረግበት፣ የሚሉትን ያጠቃልል ነበር። ከሶቪየት ህብረት መንግሥት ጋር የጦር ኃይል ለመቀነስ በ1989 ስምምነት ተደረሰና በ1991 የሶቪየት ጦር ኃይል ጠቅልሎ እንዲወጣ ተደረገ።

ልክ አሁን አገራችን ውስጥ እንደሚታየው - የምስራቅ አውሮፓ ህዝብም በነፃ እንዲሰበሰብና የፖለቲካ እንቅስቃሴ እንዲያደርግ አይፈቀድለትም ነበር። ህዝብ በነፃ እንዲንቀሳቀስ አይፈቀድለትም ነበር። ጋዜጦች በነፃ እንዲዘግቡ አይፈቀድላቸውም ነበር። ህዝብ በነፃ እንደልቡ ነፃ ጋዜጦችን እንዲያነብ አይፈቀድለትም ነበር። ህዝብ በነፃ እንደልቡ ነፃ የሬዲዮ ማሰራጫዎችን እንዲያዳምጥ ወይም የቴሌቪዥን ፕሮግራሞችን እንዲያይ አይፈቀድለትም ነበር። የኮሚኒስት ፓርቲው የሬዲዮንና የቴሌቪዥን ስርጭቶችን ይቆጣጠር ነበርና። በአጭሩ ህዝብ ከኮሚኒስት/ሶሻሊስት ፓርቲ ውጭ በነፃ የፈለገውን ሰው ወይም ሌላ ፓርቲ የመደራጀትና የመምረጥ ህጋዊ መብት አልነበረውም። መብቱ የሚሽከረከረው በተወሰኑና በቀረቡለት ምርጫዎች ዙሪያ ብቻ ነበር።

ታዲያ በ1990 ሃንጋሪ ውስጥ ለመጀመሪያ ጊዜ ነፃና ዲሞክራሲያዊ ምርጫ ተደርጎ ስድስት ፓርቲዎች አሸንፈው ወደ ፓርላማ ገቡ። እስከ 1989 ድረስ በአንድ የኮሚኒስት ፓርቲ ትመራ የነበረች አገር በ1990 ስድስት ፓርቲዎች ተመርጠው ፓርላማ ገቡ። እንዴት ስድስት ፓርቲዎች ሊመረጡ ቻሉ? ምን ያህል የፖለቲካ ፓርቲዎች ተመስርተው ነበር? የፖለቲካ ፓርቲዎች እንዴት ሊቋቋሙ ቻሉ? የምርጫ ሂደቱስ ምን ይመስል ነበር?

## የጠረጴዛ ዙሪያ ውይይት[14]

በ1989 የበጋ አጋማሽ ላይ በአገሪቱ የለውጥ እንቅስቃሴ ለማምጣትና የዲሞክራሲ ጥቅል "democracy package" ተግባራዊ ለማድረግ ሃንጋሪያውያን በጠረጴዛ ዙሪያ ተቀምጠው መወያየት ጀመሩ። በጠረጴዛ ዙሪያ የተሰበሰቡት ሃንጋሪያውያን ከተለያየ አካባቢ በሙያ ዘርፎች ልምድ ያካበቱ፤ የተከበሩ የአገሪቱ ዜጎች፤ የፖለቲካ ምሁራን፤ የሙያ ማህበራት፤ የወጣትና የሴቶች ማህበራት ወዘተ የተውጣጡ ነበሩ። እስከ 1989 የነበሩት የኮሚኒስት ፓርቲና የተለያዩ በጠባብ ፖለቲካ ዙሪያ ይታገሉ የነበሩት የህብረተሰቡ የሰራተኛና የሙያ ማህበራት፤ በስደት የሚኖሩት የፖለቲካ ፓርቲዎችም ሁሉ ተካፋይ ነበሩ።

ይህ የጠረጴዛ ዙሪያ ውይይት የተካሄደው በዓለም አቀፍ ደረጃ ሁለት አበይት ድርጊቶች በተካሄዱበት መካከል ማለትም በ3 ወራት ውስጥ ነበር። ከሰኔ /ጁን/ 1989 እስከ መስከረም /ሴፕተምበር/ 1989 ነበር። 1) ሰኔ /ጁን/ 1989 ቻይና ውስጥ ተማሪዎች የተቃውሞ ሰልፍ ሲያደርጉ በኮሚኒስት ፓርቲው የተፈጁበት ወቅት ነበር። 2) መስከረም /ሴፕተምበር/ 1989 ፖላንድ የመጀመሪያው ነፃ ምርጫ ያካሄደችበት ወቅት ነበር።

በጠረጴዛ ዙሪያ የተሰባሰቡት ሰዎች ብዛት 573 ሲደርሱ በሶስት ደረጃ ተከፍለው ነበር ስራቸውን የሚያካሂዱት። በጠረጴዛ ዙሪያ የተሰባሰቡት ሰዎች ትልቁ ኃላፊነታቸው ከሆነው መካከል፤ ህገ-መንግስት ማርቀቅ፤ የምጣኔ ሃብት ቅየሳና የፖለቲካ መድረኩን ማስፋትና የነፃ ምርጫ መዋቅርና ተቋም መዘርጋት ነበር።

መረጃዎች እንደሚያመላክቱት በዚህ ታሪካዊ በሆነው ጠረጴዛ ዙሪያ የተሰባሰቡት ግለሰቦች ማለትም ህገ መንግሥት አርቃቂው ክፍልንም ጨምሮ እንደ ግለሰብ ደረጃ ሲታዩ፤

1) ከሁሉም ማሕበረሰብ / ዘውጌ የተውጣጡ ናቸው።

2) በተለያየ የሥራ መስክ የተሰማሩና ልምድ ያካበቱ ናቸው - ማለትም ከገበሬው፤ ከነጋዴው፤ ከተማሪው፤ ከአስተማሪው፤ ከሠራተኛው፤ ከሴቶች፤ ከአዛውንቶች፤ ወዘተ የተውጣጣ ነው። እንዲሁም የወደፊቱ አገራቸው ምን መምሰል እንደሚኖርባት ባገኙት አጋጣሚ አሳባቸውን ሲያንሸራሽሩ የነበሩ ናቸው።

3) የእድሜ ክልላቸውን ስንመለከት ደግሞ፡ ሀ) አንድ ሦስተኛው በ60 ዎቹ የእድሜ ክልል ውስጥ ይገኛሉ። እንዲሁም የምዕራቡ ዓለም ባህልና የፖለቲካ ዝንባሌ ያላቸው ናቸው። በኮሚኒስቱ አገዛዝ / በሶሻሊስቱ ስርዓት ውስጥም ያለፉ ናቸው። ለ) አንድ አራተኛ የሚሆኑት በወጣት የእድሜ ክልል ውስጥ የሚገኙ ናቸው። በዚህ እድሜ ክልል ውስጥ የሚገኙት የሶሻሊስት አቀንቃኞች ቢሆኑም ግን ለውይይትና ለስምምነት ቀና አመለካከት የያዙ ግለሰቦች ናቸው።

4) በዚህ ታሪካዊ በሆነው ጠረጴዛ ዙሪያ የተሰባሰቡት ተሳታፊ ግለሰቦች የሦስት ወራት የጠረጴዛ ዙሪያው ውይይት ካጠናቀቁ በኋላ ወደ ቀደመው ስራቸው ተመልሰዋል። እንደ ሃገሪቱ ዜጋ የሚፈልጉትን ኑሮ ለመኖር ወደ ኅብረተሰቡ ተቀላቅለዋል። ከነዚህ ተካፋዮች ውስጥ እጅግ በጣም ጥቂቶቹ ብቻ ናቸው ወደ ፖለቲካው ውስጥ ገብተው ፖለቲከኞች የሆኑት።
5) ከጠረጴዛ ዙሪያው ውይይት ተሳታፊዎች ውስጥ 87% ወንዶች ሲሆኑ 13% ሴቶች ነበሩ።
6) የጠረጴዛ ዙሪያው ውይይት ተሳታፊዎች ሁሉም የተማሩ ነበሩ።

ነገርን ነገር ያነሳዋልና የሀንጋሪ ኮሚኒዝም ፓርቲ በአገሪቱ ዜጎች ዘንድ በትልቅ ውለታነቱ የሚወሳው በትምህርት ዘርፍ የነበረው ከፍተኛ የትምህርት እድገት መዋቅር ነበር። ለሁሉም ዜጎቹ እኩል የትምህርት አቅርቦት ስለነበረው በትምህርት መስክ ያበረከተው አስተዋጽዖ ትልቅ ነው። በወቅቱ ባለማጋነን እንደ ሁለተኛ ዜጋ ሆነው ከሚቆጠሩ ዜጎች (ጂፕሲዎች ይባላሉ) በስተቀር ትምህርት ያልተማረ ቢያንስ መለስተኛ ወይም ሁለተኛ ደረጃ ያልጨረሰ ሃንጋሪያዊ እጅግ በጣት የሚቆጠር ነው። ለጊዜው ስለ ትምርት ዘርፍ ይህን ያህል ካልኩኝ ወደ ዋናው ነጥቤ ልመለስ።

ሀንጋሪ በ1988 አካባቢ 21.2 ቢሊዮን የአሜሪካን ዶላር የሚቆጠር የውጭ ባለዕዳ ብትሆንም ገንዘቡ የዋለው ህዝቡን በመመገብና ትምህርትና የምጣኔ ሃብት መዋቅር እንዲስፋፋ ስለነበር መሪያቸው የነበረው ካዳር ያኖሽና እንዲሁም በወቅቱ የነበሩት ባለስልጣኖች በገንዘብ ምዝበራና በስርቆት አይታሙም ነበር። ስለሆነም ካዳር ያኖሽ በህዝቡ ዘንድ ትልቅ አክብሮትና ፍቅርን አትርፏል። አንድ መሪ የህዝብን ፍቅር ከማግኘት በላይ የሚሻው ነገር ምን አለ?

አገራችን ኢትዮጵያ በአሁኑ ሰዓት ከ30 ቢሊዮን የአሜሪካን ዶላር በላይ ባለ ዕዳ ስትሆን ዕዳው በወሮበሎች እየተጋጠ ይገኛል። ይህ ገንዘብ ለአገር ጥቅም ቢውል ኖሮ ትልቅ እድገት ምን ደረጃ እንደርስ ነበር? ለሚለው መልስ “ሮቢንሰን ክሩሶና የሕወሃት ጦርጦስ”[15] የሚለውን መጣጥፍ ይመልከቱ።

## የምርጫ መዋቅር መዘርጋት፤ የአዳዲስ ፓርቲዎች መፍላትና ምርጫ

“የዲሞክራሲ ጥቅል እንዴት ተግባራዊ ይሁን?” የሚለው ትልቁ ነጥብ ነበር። እንዲህም ሆነ። በጊዜያዊነት ለሽግግር እንዲያመች አንድ ጠ/ሚ ተመረጠ። ከ30-40 ዓመታት በፊት የተቋቋሙትና በስደት የነበሩት ተቃዋሚዎች (ግለሰቦችና ፓርቲዎች)፣ ከ30-40 ዓመታት በፊት የተመሰረቱት የሠራተኞች፣ የወጣቶችና የሴቶች ማህበራት፣ የሙያና የመምህራን ማህበራት፣ ወዘተረፈ ወደ ታች ወርደው ከህዝቡ ውስጥ ገብተው የፖለቲካ ስራዎች እንዲሰሩና እንዲሁም ማናኛውም የአገሪቱ አዳዲስ የፖለቲካ ፓርቲዎች በነፃነት እንዲመሰርቱ ተፈቀደላቸው። አስቀድመው የተደራጁትም ቢሆኑ መዋቅራቸውን በየትኛውም የአገሪቱ ክፍል እንዲያስፋፉ ተፈቀደላቸው። በነገራችን ላይ ሶሻሊስት አገራት ውስጥ እንደነዚህ ያሉ የሙያና ህዝባዊ ማኅበራት ለኮሚኒስት/የሶሻሊስት ፓርቲው እንደ ፖለቲካ ፓርቲዎች የሚጠቀምባቸው መዘውር ናቸው። ሰፋፊ መዋቅር አላቸው። ህዝቡን (ወያኔ እንደዘረጋው ዓይነት እንደ 1 ለ 5) መጠርነፊያ መሳሪያዎች ናቸው።

በወቅቱ የነበረውን የምርጫ ተቋም መጠነኛ ጥገና ተደርጎለት ማለትም በአዲስ ህግና የሰው ኃይል ተዋቀረ። የሰው ኃይል ስልጠና ሰፊ ቦታ ተሰጠው።

1) ሦስት እርከን ምርጫ

ይህ የመጀመሪያው ዲሞክራሲያዊ ምርጫ በመሆኑ ወደ ፓርላማ ለመግባት በሚደረገው ጉዞ ምርጫው ሦስት ዙር ያለው የምርጫ እርከን እንዲሆን ተወሰነ። ቀደም ባሉት ዘመናት ከ30-40 ዓመታት በፊት የተቋቋሙት የፖለቲካ ፓርቲዎች “አንጋፋ የፖለቲካ ፓርቲዎች ስለሆንን፣ የነበረን አስተዋጽኦ ከግምት ውስጥ ገብቶ፣ እኛ በቀጥታ ወደ ምርጫ መሄድ አለብን።” የሚሉ ሃሳቦችም በወቅቱ አቅርበው ነበር። የቀረበላቸው መልስ ግን “እንግዲያውስ በተዘረጋው የዲሞክራሲ መዋቅር ውስጥ ተሳትፋችሁ ጥንካሬያችሁ መፈተሽ አለበት።” የሚል ነበር። የፖለቲካ ፓርቲዎቹም “በምርጫ ቦርድ ላይ አመኔታ የለንም” የሚል መከራከሪያ ነጥብም አቅርበው ነበር። ለዚህ መፍትሔ ሆኖ የቀረበው “እንዲህ ያለ ምርጫ በአገራችን ሲደረግ የመጀመሪያ ጊዜ ስለሆነ ልምድ ለማካበት አገሪቱ ውስጥ ያሉትን ታማኝና ታዋቂ ግለሰቦችን እንዲሁም በተጨማሪ የምዕራቡን አገራት የምርጫ ታዛቢዎች በየምርጫ ጣቢያዎች ተገኝተው

እንዲታዘቡ፤ አንድ ዓይነት ጉድለት ቢገኝ ግን ቅጽበታዊ እርምጃ የሚወስድ አንድ ቡድን በምርጫ ቦርድ ውስጥ እንዲቋቋም ተወሰነ።”

ቀደም ብለው የተደራጁትና በዕቡህ ውስጥ ለውስጥ ትግል ሲያካሄዱ የነበሩት ፓርቲዎችም ሦስት ዙር ያለው የምርጫ እርከን ውስጥ ማለፍ የነበረባቸው የዲሞክራሲን ባህል እንዲለምዱና “እኛ ብቻ ታግለን” በሚል ፉከራ እንዳይታበዩ፤ በትረ ስልጣኑን በአንድ ምርጫ አሸንፌው ቢጨብጡም አገሪቷ ላይ ሌላ የፖለቲካ ጣጣ እንዳያመጡ በሚል አስተሳሰብ የተፈጠረ የምርጫ እርከን ነበር። አዲስ የተፈለፈሉት ወይም ቀደም ብለው ተፈጥረው በዚህ ምርጫ የተመዘገቡት ፓርቲዎች ሁለት የአካባቢና አንድ አገራዊ የምርጫ እርከን ማለፍ ይጠበቅባቸዋል። መጀመሪያ በቀበሌያቸው ሁለተኛ በአውራጃ ሦስተኛው ደግሞ አገር አቀፋዊ ደረጃን የያዘ የምርጫ መዋቅር ነበር። የዚህ ዓይነት የምርጫ እርከን የሚጠቀመው አነስተኛ የማህበረሰብ ክፍሎችም በፖለቲካው ውስጥ ድምፃቸውን እንዲያሰሙ እድሉን ለመክፈት ነው። ሃንጋሪ ውስጥ 13 የማህበረሰብ ክፍሎች ስላሉ ሁሉም ድምፃቸውን ማሰማት እንዲችሉ በማለት የተዘጋጀ ፖለቲካዊ መፍትሔ ነው።

2) የፖለቲካ ፓርቲዎች ተፈለፈሉ

<u>በዚህም መሠረት ግዙፎቹ አንጋፋ የፖለቲካ ፓርቲዎቹን ጨምሮ ወደ 100 የሚደርሱ የፖለቲካ ፓርቲዎች ተመሠርተው ለምርጫ ተመዘገቡ።</u> ለዚህ እንዲረዳቸው ለሚመሰረቱት የፖለቲካ ፓርቲዎች የገንዘብ እርዳታና፤ የመሰብሰብ፤ በአገሪቱ ማንኛውም ክፍል ተንቀሳቅሰው ቅስቀሳ እንዲያደርጉ፤ ወዘተ መድረኩ ተከፈተላቸው። የፖለቲካ ፓርቲዎች በዘውጌ (ለምሳሌ የይሁዳውያን ወይም ጀርመናውያን ዝርያ ባላቸው)፤ በህብረ ብሔር፤ በኃይማኖት (ለምሳሌ የክርስቲያን ፓርቲዎች) በፆታ ወይም ማሕበረሰብ ክፍል (ለምሳሌ የወጣቶች) ወዘተ አመቺ በሆነ መንገድ በስፋት እንዲቋቋሙ ተፈቀደ። በተጨማሪም ቀደም ባሉት 40 እና 50 ዓመታት ውስጥ የተቋቋሙት ፓርቲዎችም ሙሉ በሙሉ ያለገደብ እንዲንቀሳቀሱ ተፈቀደላቸው። በተሰጣቸው ጊዜ ውስጥ የፖለቲካ ድርጅታቸውን ፕሮግራምና ያላቸውን የምጣኔ ሃብት፤ ሌሎች የአጭርና የረጅም ጊዜ እቅዶቻቸውን ለህብረተሰቡ አመቺ በሆነ መንገድ ሁሉ ማለትም በስብሰባ፤ በአደባባይ በመቀስቀስ፤ በዜና ማሰራጫዎች ወዘተ ተጠቅመው ስልጣን ላይ ቢወጡ ምን እንደሚያደርጉ አስረድተው የህዝብ ድምፅ ለማግኘት ከፍተኛ ፉክክር አደረጉ። በዕቡእ ይንቀሳቀሱ የነበሩት የፖለቲካ ድርጅቶችም የህዝብ ድምፅ ለማግኘት በነፃ መንቀሳቀስ ቻሉ።

ለ10 ሚሊዮን ህዝብ ወደ 12000 የሚደርሱ የምርጫ ጣቢያዎች ነበሩ። በእያንዳንዱ ምርጫ ጣቢያ ከ750 እስከ 800 መራጮች አሉት ማለት ነው። በየምርጫ ጣቢያዎች በቂ ታዛቢዎች ማሰማራት ተችሎ ነበር። የውጪም ሆነ የአገር ውስጥ ታዛቢዎች ለቁጥጥር ምንም ዓይነት ገደብ አልተጣለባቸውም ነበር። በየምርጫ ጣቢያዎች እንደልብ እየተዘዋወሩ የምርጫ ስርዓቶችንም ሆነ የምርጫ ካርዶች ቆጠራ ታዝበዋል። <u>የአገር ውስጥም ሆነ የውጪ አገር ታዛቢዎችም በሁሉም የእርከን ደረጃ ምርጫው ሰላማዊና በምርጫ ሂደቱም ምንም ዓይነት እንከን ያልታየበት ነፃና ዲሞክራሲያዊ ምርጫ እንደነበር ዘግበዋል።</u> ሃንጋሪያውያን አዲስ የዲሞክራሲ የታሪክ ምዕራፍ ከፈቱ።

## የፖለቲካ ፓርቲዎች ምርጫ ውድድር

የአካባቢ ምርጫ - 100 የፖለቲካ ፓርቲዎች ተወዳደሩ።

የመጀመሪያ ዙር የምርጫ ውድድር እንዴት እንደተካሄደ ለማስረዳት እንዲረዳኝ ቁጥሮችን በምሳሌ ልጠቀም ፈለግሁ። (ቁጥሮቹ በሙሉ የኔ ምሳሌዎች ናቸው። በአንድ ወረዳ/አውራጃ እስከ 5 የፖለቲካ ፓርቲዎች ይወዳደራሉ እንበል።) የመጀመሪያ ምርጫ የተካሄደው በወረዳ ደረጃ ሲሆን እነዚህ ፓርቲዎች በተመሰረቱበት ወረዳ አካባቢ ምርጫ አድርገው ከ25% - 30% ድምፅ ያገኙት በቀጥታ ወደሚቀጥለው እርከን ያልፋሉ። ከ20% - 24.99% ድምፅ ያገኙት ግን እየተዋሃዱ የምርጫውን ነጥብ 30% በሚሟላት ወደሚቀጥለው እርከን እንዲያልፉ ተደረገ። የፖለቲካ ፓርቲዎቹ ሲዋሃዱ መርሃ ግብራቸውም አብሮ ይዋሃዳል። አንባቢዎች ልብ እንዲሉ የምፈልገው <u>ትክክለኛ የፖለቲካ ፓርቲዎች ጥምረትም ሆነ ውህደት የሚፈፀመው እንደዚህ ያሉ ትክክለኛ “ሁኔታዎች” ሲፈጠሩ ብቻ ነው። ከላይ ለመጠቆም እንደሞከርኩት</u>

<u>የፈረሱ ከጋሪው በፊት የመሆኑ ሁኔታ መቅደም ይኖርበታል። ቀዳሚ የሆኑት "ሁኔታዎች" ነፃ የሆነ የምርጫ ቦርድ፤ ነፃ የመሰብሰብ መድረክ፤ ነፃ የመደራጀት መድረክ፤ በነፃ ሃሳብን የመግለፅ መድረክ ወዘተ ሲሆን ጥምረት እና ውህደት ስምረት ይኖረዋል።</u> በዚህም መሠረት ለአውራጃው የምርጫ እርከን ያለፉት የፖለቲካ ፓርቲዎች ቁጥር ከ100 የፖለቲካ ፓርቲዎች ወደ 50 የፖለቲካ ፓርቲዎች ወረዱ። ማለትም 50 የፖለቲካ ፓርቲዎች ለሚቀጥለው ውድድር አለፉ።

የአውራጃ ምርጫ- 50 የፖለቲካ ፓርቲዎች ተወዳደሩ።

ሁለተኛው የአውራጃ ምርጫ ደግሞ የሚካፈሉት 50 የፖለቲካ ፓርቲዎች ለመጨረሻው አገራዊ ምርጫ ለማለፍ የሚጠበቅባቸው 30% ድምፅ ማግኘት ነበር። በምርጫው መሠረት 25% - 30% ያገኙት በቀጥታ ወደሚቀጥለው እርከን ያልፋሉ። ከ20.00% - 24.99% ድምፅ ያገኙት ግን እየተዋሃዱ የምርጫውን ነጥብ 30% በሚሟላት ወደሚቀጥለው እርከን እንዲያልፉ ተደረገ። በዚህም መሠረት ለአገር አቀፋዊ የምርጫ እርከን ያለፉት የፖለቲካ ፓርቲዎች ቁጥር ከ50 ወደ 12 ወረደ።

አገራዊ ምርጫ - 12 የፖለቲካ ፓርቲዎች ተወዳደሩ።

ሦስተኛው አገር አቀፋዊ ምርጫ ደግሞ የሚካፈሉት 12 የፖለቲካ ፓርቲዎች ለመጨረሻው አገራዊ ምርጫ ለማሸነፍ የሚጠበቅባቸው በ8% - 13% ድምፅ ማግኘት ነበር። በአገራዊ ምርጫው ህግ መሠረት ከ8% በላይ ያገኙት 6 የፖለቲካ ፓርቲዎች ወደ ፓርላማ ገቡ።


## የታዋቂ ምሁራንና የአገር ሽማግሌዎች ድርሻ

እዚህ ላይ አንድ መነሳት የሚገባው ነጥብ አለ። ይኸውም ቀደም ብለው በእቡዕ ተደራጅተው ሲታገሉ የነበሩት የፖለቲካ ፓርቲዎች እንደገና ድርድሩ ላይ ሲቀመጡ የኮሚኒስት ፓርቲው ቃሉን አጥፎ ከፍተኛ እንግልት ይደርስብናል የሚል ፍራቻ ነበራቸው። በኮሚኒስት ፓርቲው ላይም "እምነት" የሚባል ነገር ፈፅሞ አልነበራቸውም። በድርድሩ ላይም ቢሆን "እኛና እነሱ" "እነሱና እኛ" በሚል ጎራ ከፍተኛ የሆነ ትንቅንቅ ውስጥ ገብተው ነበር። እውነቱን ለመናገር የጦር መሳሪያ ይዘው ቢሆን ኖሮ ሌላም ደረጃ በተዳረሱ ነበር። (በነገራችን ላይ የዚህ ፅሁፍ አቅራቢ ይህ ሽግግር በሚካሄድበት ጊዜ ሀንጋሪ ውስጥ ነዋሪ ነበር።) ታዲያ ይህንን ችግር ለማቃለል የታወቁ ምሁራንና የአገር ሽማግሌዎች የተጫወቱት ሚና እጅግ ከፍተኛ ነው። የአገር ሽማግሌዎችም ሚና በኮሚኒስት ፓርቲ ዘመን የኮሚኒስት ፓርቲውን "ጥቅም" እስካልነካ ድረስ የሚል ገደብ ነበረው። (ልክ አሁን በሕወሃት ዘመን እንደምናየው "የአገር ሽማግሌዎች የማይሰሙበት ዘመን" "የአገር ሽማግሌዎች የማይከበሩበት ዘመን" ማለት ነው።) የአገር ሽማግሌዎች በነፃ ሃሳብ የማንሸራሸር ችግር ነበረባቸው፤ በተጨማሪም በኮሚኒስት ዘመን ሽማግሌዎች ፈፅሞ አመኔታ አልነበራቸውም ነበር። ሆኖም ግን በዲሞክራሲያዊ የሽግግር ወቅት ሁለት አራምባና ቆቦ አቋም ይዘው የቀረቡትን የፖለቲካ ፓርቲዎች ለማስታረቅ ታዋቂ ምሁራንና የአገር ሽማግሌዎች የተጫወቱት ሚና በተለይም ዘላቂ እርቅ እንዲሰፍን የአስታራቂ አሳቦችን በማመንጨት በኩል ከፍተኛ ሥራ ሰርተዋል። <u>ዲሞክራሲ ባለበት ቦታ ታወቂ ምሁራንና የአገር ሽማግሌዎች በነፃ አሳባቸውን በማንሸራሸር በአገርም ሆነ አስፈላጊ በሆነ ቦታ ሁሉ እርቅን ለማውረድ ችሎታ አላቸው።</u>

እንግዲህ ይህንን መንገድ በመከተል በ1990 ሀንጋሪ የመጀመሪያውን 6 ፓርቲዎች በመምረጥ ፓርላማ ገቡ። ላለፉት 24 እና 25 ሃንጋሪ ዓመታት የተረጋጋ መንግስታዊ የፖለቲካ ስርዓት መሰረተች። ህዝቡ የፈለገውን ይመርጣል ያልፈለገውን በምርጫ ሳጥን በትረ ስልጣኑን ይነሳል፤ ሃንጋሪያውያን ሃሳባቸውን ያለምንም ተፅህኖ ይገልፃሉ። የተረጋጋ መንግስታዊ መዋቅር መፍጠር ይቿል እንዲህ ነው። የተቀሩት የምስራቅ አውሮፓ አገራትም ይህንን የሃንጋሪያውያንን መንገድ በመከተል ወይም አነስተኛ ጥገና በማድረግ ወደ ዲሞክራሲ ጎዳና አቀኑ።

ምስራቅ አውሮፓውያን ከ"አብዮታዊ ዲሞክራሲ" ተውሳክ የተገላገሉት በዚህ ዓይነት የዲሞክራሲያዊ ሽግግር መንገድ ነው። የራሺያና የቻይና "አብዮታዊ ዲሞክራሲ" ተውሳክ የሚያሽረው ኮሶው (መድኃኒቱ) የምስራቅ አውሮፓውያን ወደ "ዲሞክራሲያዊ" የፖለቲካ ሽግግር የተካሄደበት መንገድ ነው። ከአንድ ፓርቲ ፍፁማዊ አገዛዝ ወደ ህዝባዊና ዲሞክራሲያዊ የአስተዳደር የምስራቅ አውሮፓውያን ያመሩት በዚህ ዓይነት መንገድ ነበር።

**የምሥራቅ አውሮፓውያን የአስተዳደር መዋቅር ከ1990 እ. አ. አ. በኋላ**




መራጮች የሚፈልጉትን ግለሰብ በዲሞክራሲያዊ መንገድ በምርጫ ካርድ መምረጥ ይችላሉ።

## የፖለቲካ ልምድ ትምህርት

ከታሪክ እንደምንማረው የአገራት የፖለቲካ አስተዳደር ልምድና መዋቅር ተወራራሽ ነው። ሁለት ተፃራሪ የፖለቲካ አስተዳደር ልምዶችን ልጥቀስ፤

በአንድ በኩል የአፍሪካ አገራት የጨካኙን አስተዳደር ከገረሰሱ በኋላ በልምድ እጦት ምክንያት የአገራቸውን ፖለቲካና የዲሞክራሲ ችግር ለማስተካከል የተቸገሩ ብዙ የአፍሪካ አገራት አሉ። በምሳሌነት ሊቢያን መጥቀስ ይቻላል።

በሌላ በኩል ደግሞ ከሶሻሊዝም/ ኮሚኒዝም የሶቪየት ህብረት ቀንበር ስር ነፃ የወጡት ምስራቅ አውሮፓውያን (ለምሳሌ ፖላንድ፤ ሃንጋሪ፤ ምስራቅ ጀርመን) ከአጀማመሩ አንስቶ እጅግ በጣም የተዋጣለት የዲሞክራሲ ለውጥ የዜጎቻቸውን ደም በከንቱ ሳይፈስ አካሂደዋል። እንደዚህ ያሉ የምስራቅ አውሮፓውያን አገራት እንዴት የዲሞክራሲ ለውጥ እንዳደረጉ መማማሩና ትምህርት መቅሰሙ እንዲሁም ሌሎች የአፍሪካ አገራት ከወደቁበት አዘቅት ውስጥ እንዳንገባ ይረዳናል።

አገራችን ኢትዮጵያ ከ1966ቱ ህዝባዊ እንቅስቃሴ መክሽፍ በኋላ የተሻለ የፖለቲካ ልምድ ከዓለም መድረክ መማር እንችላለን። ሕወሃት እንደሌላው ስርዓት በስብሶ በመውደቅ ከገደል አፋፍ ላይ ይገኛል። ከሕወሃት የምትተላለፈውም አገር ሁሉ ነገሯ ተግጦና በዕዳ የተዘፈቀች አገር ናት። በሁሉም መስክ አገሪቷን ለመገንባት እጅግ በጣም ከባድ እንደሚሆንና ጊዜ እንደሚወስድ እሙን ነው።
ታዲያ "በፖለቲካው መስክ" እኛ ኢትዮጵያውያን ከነዚህ የምስራቅ አውሮፓውያን የፖለቲካና የመንግስት መዋቅር መዘርጋት ሂደት ምን እንማራለን?

ሀ) ወደ ዲሞክራሲ ጎዳና ለማቅናት "የዲሞክራሲ ሽግግር" መኖር አስፈላጊ ነው። በተለይም በአሁኑ ዘመን ከሕወሃት መውደቅ በኋላ "የዲሞክራሲ ሽግግር" ለማድረግ አንድ አገር አቀፍ የሆነ፣ የጠረጴዛ ውይይት መድረክ ማዘጋጀት ወቅቱ ግድ ይላል። በዚህ "የዲሞክራሲ የሽግግር ሂደት" ውስጥ ተአማኒነትና ተቀባይነት ያላቸው ታዋቂ ምሁራንና የአገር ሽማግሌዎች፣ ወጣቶች፣ ሰራተኞች፣ ገበሬዎች፣ ወዘተ ከየአካባቢው እየተወከሉ መዋተው የፖለቲካውንና የምጣኔ ሃብትና የምርጫ መዋቅር ዘርግተው፣ ህገ-መንግሥት አርቅቀው ተመልሰው ወደ ቀደመው የሥራ ቦታቸው እንዲመለሱ የሚደረጉበትን አመቺ ሁኔታ መፍጠር ያስፈልጋል። ተወካዮቹ ሥራቸውን ጨርሰው ለምን ወደ ቀደመው የስራ ቦታቸው ይመለሳሉ? አጭሩ መልስ የሚያወጡት የፖለቲካ ህግ "የጥቅም ግጭት" እንዳያመጣ ነው።

ይህ ከሁሉም የህብረተሰብ ክፍል የተውጣጣ ጊዜያዊ (የጊዜ ገደብ ተቀምጦለት ከ3-6 ወራት የሚቆይ) የውይይት መድረክና የአስተዳደር ስርዓት ይመሰርታል። በሚከተሉት ነጥቦች ዙሪያ እቅድ እንዲነድፍ ይደረጋል፣ የፖለቲካ ፖሊሲ፣ የምጣኔ ሃብት ፖሊሲ (የመሬት ይዞታ፣ የውጭ ብድርና ዕዳ፣ ወደ ውጭም ሆነ አገር ውስጥ የተዛወሩትን የመንግስት ንብረትን የሚፈትሽ፣ ፍትህ ለተፈናቀሉ፣ ለተገፉ ዜጎች፣ ያለ አግባብ ለበለፀጉ ግለሰቦች፣ ያለ አግባብ የተፈረሙ አለም ዓቀፋዊ ውሎችንና የተዘረፉ መሬቶችና ንብረቶች የሚመለሱበትንና በመደራደር የሚፈቱበትን መንገድ ለመሻት፣ ወዘተ)፣ ህገ-መንግስት ማርቀቅ፣ የምርጫ ውድድር መድረኩን ህግና ደንብ የሚያረቅ፣ የመሳሰሉትን የአጭርና የረጅም ጊዜ እቅዶችን እንዲሁም አገራዊ የፖሊስና የወታደራዊ (ጦር ሰራዊት) መዋቅርን መንደፍ ይጠበቅባቸዋል። እንደሚታወቀው የጦር ሰራዊቱን የሚያዘው (የሚቆጣጠረው) ክፍል ወይም ግለሰብ አገሪቱን ወዳልተፈለገበት አቅጣጫ እንዳይመራት መዋቅር መዘርጋትና ህገ-መንግስቱ ላይ መረቀቅ ይኖርበታል። አንድ ነገር አስረግጬ ላስምርበት ህገ-መንግስት መረቀቅም ሆነ መፅደቅ ያለበት በአገሪቷ ነዋሪዎች እንጂ በፓርቲ መሪዎች ወይም ስልጣን ላይ ባሉ ግለሰቦች ሊሆን አይገባውም። ህዝብ አለቃ ነው። ህዝብ ህገ-መንግስቱን ያረቃል። ህዝብ የሚበጀውን ይሾማል። ህዝብ የማይጠቅመውን ይሽራል።

ለ) የዲሞክራሲ ባህልን ለማዳበር በመጀመሪያዎቹ ሁለትና ሦስት ዙር ምርጫዎች - አራት ደረጃ (ቀበሌ፣ ወረዳ፣ አውራጃ፣ ክ/ሃገር)[16] ያላቸው የምርጫ መዋቅር ማዘጋጀት። ማንኛቸውም የፖለቲካ ፓርቲዎች (ቀደም ብለው የተመሰረቱትም ሆነ መሳሪያ የታጠቁት ወይም በሰላማዊ መንገድ የሚታገሉት፣ ወይም ወደፊት አዲስ የሚፈጠሩት) ሁሉም በህዝቡ የምርጫ እሳት ተፈትኖ ማለፍ እንዳለበት፣ በተለይም በምርጫ እርከኖች በኩል ማለፍ ይጠበቅበታል።

ሐ) ግብፅ ውስጥ እንደታየው ዓይነት የፖለቲካ አወዳደቅ አገራችን ውስጥ እንዳይደገም ለማስቀረት። ይኸውም የሙስሊም ወንድማማቾች ፓርቲ ለ80 ዓመታት ውስጥ ለውስጥ ታጋድሎ ነው የመጣው። ነገር ግን ሙሉ ስልጣኑን በምርጫ ከተረከበ በኋላ ዳግማዊ ሙባረክ ለመፍጠር ከጀለ፣ በኅብረተሰቡ ተመርጦ ግን ለኅብረተሰቡ ስሞታ ማዳመጫ ጆሮና ፍላጎት ያጣ ስለነበር ስልጣኑን ሊያጣ ቻለ። አንድ የፖለቲካ ፓርቲ ስልጣኑን ከያዘ በኋላ፣ የጦር ሰራዊት፣ የፖሊስና የደህንነት፣ የኢኮኖሚ መዋቅሩን ጨብጦና ተደላድሎ ሥልጣኑን የሙጥኝ ብሎ እንዳይጣበቅ ለመከላከል የሚያስችል ህግ ማዘጋጀት። እሳት የላሱ ወይም ጉልበተኛ ፖለቲከኞች ቀላል መንገድ በመፍጠር ያሻቸውን ማድረግ የማይችሉ መሆናቸውን እንዲሁም ህግ የሰፈነባት አገር ለመዘርጋት። እንዲሁም ህገ-መንግስቱን ለመለወጥ ለምሳሌ በአፍሪካዊቷ አገር በብሩንዲ እንደምናየው እንደ ፕሬዝዳንት ንኩሩንዚዛ ያለ ጉልበተኛ መሪ[17] (የጦር ኃይሉንና ወታደራዊውን ክፍል ስለሚያዝ ብቻ) ለ3ኛ ጊዜ ለመመረጥ የሚያስችለውን የህገ-መንግስት ደንብ በማሻሻል ሊመረጥ በቅቷል። ህገ መንግሥቱንም አሻሽሎ ለመጪው 30 ዓመታት ስልጣን ላይ ለመቆየት እያመቻቸ ይገኛል። ከዚህ የምንማረው ምንድነው? እንደዚህ ያሉ የህገ መንግስቱ ድንጋጌዎች እንዳይሻሻሉ ገደብ መጣል ግድ ይላል።

መ) ታዋቂ ምሁራንና የአገር ሽማግሌዎች አክብሮት የሚያገኙት ነፃ የሆነ መድረክ ሲፈጠር ብቻ ነው። በሕወሃት ዘመን አስተዳደሩ ታዋቂ ምሁራንና የአገር ሽማግሌዎችን በማቃለል በኅብረተሰቡ ዘንድ ተቀባይነት እንዳይኖራቸው ለማድረግ ከፍተኛ ጥረት እያደረገ ይገኛል። ሆኖም ግን ከላይ ለማሳየት እንደሞከርኩት ነፃ የሆነ መድረክ ስላልተፈጠረላቸው ከአነሳሳቸው ጀምሮ የሕወሃትን ዓላማ ብቻ እንዲያራምዱ ተፅህኖ ስለሚደረግባቸው ትክክለኛ የሆነ መስመር ለመከተል ያዳግታቸዋል። ነፃ የሆነ መድረክ ከተፈጠረላቸው በእንደዚህ ያለ የዲሞክራሲ ሽግግር ወቅት ሚናቸው እጅግ በጣም ከፍተኛ ነው። ከአገራችን የሽምግልና ደንብና ልምድ እንደታየው ታዋቂ ምሁራንና የአገር ሽማግሌዎች አገራቸው ውስጥ ዘላቂ ሰላም እንዲሰፍንና በሰላም እንድትኖርና ለልጅ ልጆቻቸውም አገራዊ ቅርስ ለማስተላለፍ እንደሚፈልጉ የታወቀ ነው። በተጨማሪም ታዋቂ ምሁራንና የአገር ሽማግሌዎች ህግን ተከትለው ስለሚንቀሳቀሱ ውጤቱ አመርቂ ሊሆን ይችላል።

ሠ) ለወደፊቱ የበሰለና አርቀው የሚያስቡ መሪዎችን ለማፍራት የአመራርና የስልጠና ትምህርት ማስፋፋት። በተጨማሪም አገራችን በባህል የደመቀች በተለያዩ ኅብረተሰብ ያጌጠችውን ያህል ህግና ግለሰባዊ ነፃነት የሰፈነባት እንድትሆንና ዜጎች የህግን የበላይነት መሰረት ለመጣል ይረዳታል።

## የኢትዮጵያ ታሪካዊ የነገሥታት አስተዳደር

በደርግም ሆነ በሕወሃት ዘመን የተመረጡትን ወይም የተሾሙትን ፕሬዘዳንቶች ያላቸው የስልጣን ደረጃ እስከምን ደረጃ እንደሆነ እያሰብን የአገራችንን የኢትዮጵያ ቀደም ያለውን የፖለቲካ መዋቅርና ታሪክ በአጭሩ ላንሳ።

ኢትዮጵያ ላለፉት ብዙ ሺህ ዓመታት የምትተዳደረው በንጉሳዊ የዘውድ አስተዳደር ነበር። ከክርስቶስ ልደት በፊት 5500 ዓመት ከክርስቶስ ልደት በኋላ 1967 ዓመታት በድምሩ ለ7467 ዓመታት የተዳደረችው በንጉስ ነበር[18]። ታዲያ ይህንን የዘውድ አገዛዝ እንደነበር ልንክደው፣ ልንከልሰው፣ ልንሽረው፣ ልንቀለብሰው፣ ልንሸሽገው፣ ልንዋሸው፣ ልናንቋሽሸው አንችልም። ታሪክ ያጋልጠናልና። የጀርመኑ ካርል ማርክስ ፍልስፍና ወደ አገራችን ከገባ ካለፉት 40 ዓመታት ወዲህ የንጉሣዊ አገዛዝ እንደ እፉኝት ተናዳፊ አድርገን እንድናየው ማርክሳዊ ሌኒናዊ ቅርፅ ፈጥረውለት ትውልዱን ሲግቱት ኖረዋል። ይህ ስለ ንጉሣዊ አገዛዝ ከማርክሲዝም ፍልስፍና ጋር የተጋጨው በሶቭየት ህብረት ውስጥ ሲሆን በሌኒን የሚመራው የቦልሼቪክ ፓርቲ የንጉሣዊ አገዛዙን ገርስሰው በትረ መንግስቱን በ1917 ዓ. ም. ከጨበጡ በኋላ ነው። የሚገርመው ግን ስልጣኑን የጨበጡት የቦልሼቪክ ፓርቲ መሪዎች - የፖለቲካ ፓርቲውን ስም በመቀያየር “የህዝብ አስተዳደር” በሚል ህዝቡን መብቱን ነፍገውት ላለፉት 98 ዓመታት እያስተዳደሩት ይገኛሉ። ታዲያ የቦልሼቪክ ፓርቲ መሪዎች የህዝቡን መብት የሚነፍጉ ከሆነ ቀድሞ ከነበረው ከዛሩ ወይም ከንጉሡ አስተዳደር በምን ተሻሉ? ሰፊ ጥናት የሚያሻው ይመስላል።

ታዲያ በሶቭየት ህብረት አምሳል የተፈጠሩት ኢትዮጵያ ውስጥ የበቀሉት የማርክሲስት ሌኒንስት ፓርቲዎች ንጉሣዊ አስተዳደርን ከፊውዳላዊ አስተዳደር ጋር በማጣበቅ እስካሁን ሲያስተምሩ ወይም ሲሰብኩን ይገኛሉ። ሀቁ ግን ወዲህ ነው። ለምሳሌ በዘመናችን ያለውን የአውሮፓውያን አስተዳደር በምሳሌነት ላንሳ።

## በዘመናችን የንጉሣዊ አስተዳደር በሰለጠኑት አገራት

በዓለማችን ሰልጥነዋል የተባሉትና ከአንድ እስከ ሁለት ሺህ ዓመታት በላይ እድሜ ያላስቆጠሩት አገራት በዘመናችን በዲሞክራሲ አሰራር የሚደነቁት አውሮፓውያን ለምሳሌ እንግሊዞች፣ ስዊድናውያን፣ ኖርዌያውያንና፣ እስፔናውያን ያለፉበትን የታሪክ ጎዳናና የዘውድ አስተዳደር አሽቀንጥረው በመጣል ሳይሆን "የዘውድ አስተዳደርን" እንደ ትውልድ ቅርስ በመያዝና በመንከባከብ እስከ አሁኑ ትውልድ ድረስ አቆይተውታል። ታዲያ እነዚህ ንጉሣዊ አስተዳደር የሰፈነባቸው የአውሮፓ አገሮች በርግጥ ፊውዳላዊ ስርዓት የሰፈነባቸው ናቸው?

ምዕራብ አውሮፓውያን ብልጦች ናቸው። በተጨማሪም አውሮፓውያን አገሮች የዘውድ አገዛዝን በቅርስነት ማቆየታቸው ብቻ በራሱ አርቀው ቅርስ ከትውልድ ወደ ትውልድ ለማውረስ የሚተጉ መሆናቸውን ያረጋግጣል። ቅርስን ለመጪው ትውልድ እንዲተላለፍ ማድረግ እንደ መታደልም አድርጌ እቆጥረዋለሁ። ቀደም ባለው ዘመን በርግጥም እንደ ወቅቱ ሁኔታ ነገሥታቶች ፍፁም ስልጣን ነበራቸው። አሁን ግን በአውሮፓ የነገሡት ንገሥታቶች የነበራቸው የጦር ሰራዊት፣ የፖሊስና ደህንነት እንዲሁም የኢኮኖሚ ተፅህኖዎች በዲሞክራሲ ህግ ተቀንሶባቸው በኅብረተሰቡ ውስጥ እንደልባቸው እየተንቀሳቀሱ፣ እንደ ነፃ ዜጋ እየኖሩ፣ በክብር የተመደበላቸውን መንግስታዊ ሥራ እየሰሩ ይኖራሉ። በነዚህ አገራት ውስጥ የጦር ሰራዊት፣ የፖሊስና የደህንነት እንዲሁም የኢኮኖሚ አውታር የዕለት ተዕለት ሥራ የሚቆጣጠሩት የህዝብ ተወካዮች ናቸው እንጂ ንጉሦቹ አይደሉም።

የዘመናችን የአውሮፓ ነገሥታቶች ህዝባቸውንና ወገናቸውን አክባሪ፣ ለአገሮቻቸው ቅን አሳቢ፣ ለአገሮቻቸው እድገት የሚተጉ፣ ለአገሮቻቸው ዳር ድንበር መከበር ተቆርቋሪ፣ በአገሮቻቸውም ሰላምና እርጋታ እንዲሰፍን ዋና ተዋናይ፣ ሆነው ይታያሉ።

በሌላ በኩል ደግሞ አሜሪካኖች ንጉሳዊ አስተዳደር አልነበራቸውም። ስለዚህ ላለፉት 200 ዓመታት እየተዳደሩ ያሉት በፕሬዝዳንት፣ በምክር ቤትና በህግ መምሪያ ክፍል የአስተዳደር ስርዓት ነው።

ታዲያ ከነዚህስ ከአውሮፓውያን ንጉሣዊ የዘውድ አስተዳደር ምን እንማራለን?


## አሻንጉሊት ፕሬዝዳንት ወይስ ታሪክ ጠባቂ ንጉሥ

ከላይ ለመጥቀስ እንደሞከርኩት በሕወሃት የተመረጡት ፕሬዝዳንቶች ያላቸው የስልጣን ደረጃ ስናስብ ይህንን ስልጣን በአገራችን ኢትዮጵያ ውስጥ ንጉሦች ቢሰሩት፣ ቢመሩት ለአገራችን ኢትዮጵያ የወደፊት ትውልድ ትልቅ ክብር ነው። በስም ብቻ የተቀመጡት ፕሬዝዳንቶች ስልጣን ላይ መቀመጣቸውን እንጂ እንደ ንጉሣውያን ለአገርና ለወገን ተቆርቋሪ አይደሉም። በስም የተቀመጡት ፕሬዝዳንቶች ለፓርቲያቸው እንጂ ለአገር ጥቅም ደንታ የላቸውም። ይህንን በአሁኑ የህወሃት ዘመን እያየን ስለሆነ ብዙ ምሳሌ መጥቀሱ አስፈላጊ አይመስለኝም። አሁንም አስረግጬ የምለው ነገር ቢኖር በአገራችን ኢትዮጵያ አሻንጉሊት "ፕሬዝዳንቶች" የሚሰሩት ስራ በዘውድ ንጉሥ (ማለትም የጦር ሰራዊት፣ የፖሊስና ደህንነት እንዲሁም የኢኮኖሚ የሚኖራቸው ተፅህኖ በህግ ተቀንሶባቸው) ቢሰሩት፣ ቢመሩት ለአገራችን ለኢትዮጵያ ትልቅ ክብር ነው። ለወደፊቱ ትውልድም ትልቅ ታሪክ ማቆየት ነው። እየጠፉ ያለው ባህላችንንና ታሪካችንን መልሰን በማያዳግም ሁኔታ ቦታው ላይ ማስቀመጥ መቻል የዚህ ትውልድ ግዴታ ነው።

ስለዚህ የሚከተሉትን አማራጮች - የአስተዳደር ዓይነቶችን አቀርባለሁ።


አማራጭ ፩

ኢትዮጵያ ውስጥ በአሁኑ ወቅት መንገድ አመላካች መሪ ያጣንበት ወቅት ደርሰናል። ኢትዮጵያ አንድ ተቆርቋሪ መሪ ለማግኘት በዚህ ዘመን ባትሪ ፈልጋ ማግኘት ግድ የሚላት ወቅት ደርሳለች። የዲሞክራሲ ሽግግር በማካሄድ አዳዲስ መሪዎችን ለማፍራት የተወሰኑ ዓመታት ሊፈጅ ይችላል። ስለዚህ የዘውድ አገዛዝ መሪዎች ካላቸው ልምድ አንጻር ይህንን የአመራር ክፍተት ለመድፈን ሚና ሊጫወቱ ይችላሉ። ስለሆነም እንደ መጀመሪያ አማራጭ የሚታየኝ በህገ-መንግሥት የስልጣን ገደብ ተጥሎባቸው (ማለትም የጦር ሰራዊት፤ የፖሊስና ደህንነት እንዲሁም የኢኮኖሚ የሚኖራቸው ተፅህኖ በህግ ተቀንሶባቸው) አገራችንን በማረጋጋት ስራ ላይ የሚያተኩሩበት መንገድ ቢፈለግ። ይህንን "የተጣመረ መንግስት የአስተዳደር መዋቅር" መንገድ በአሁኑ ጊዜ ሰልጥነዋል የተባሉት ምዕራብ አውሮፓውያን ከሁለተኛው ዓለም የጦርነት አዘቅት ለመውጣት ተጠቅመውበታል። ነገር ግን መራጩ ህዝብ የአካባቢ ተወካዮቹን (በቀበሌ፤ በወረዳ፤ በአውራጃና በክ.ሃገር ደረጃ) ይመርጣል።




አማራጭ ፪

ህዝቡ ርእሰ ብሄሩንና የአካባቢ ተወካዮቹን (በቀበሌ፤ በወረዳ፤ በአውራጃና በክ.ሃገር ደረጃ) ይመርጣል። ርእሰ ብሄሩ የአገር ማስተዳደሩን ስራ ይሰራል።



## ማጠቃለያ

ኢትዮጵያችን በጭላንጭል ማለት የወደፊቷ አገራችን ልትገነባው የሚገባው የአስተዳደር ዓይነት ሁሉንም ኢትዮጵያዊ ዜጋ ያካተተ መሆን ይገባዋል። የአስተዳደር አማራጭ ኖሮ አገራችንን ወደፊት ራሷን ችላ በእግሯ የምትቆምበትን ሁኔታ መፍጠር ግድ ይላል። አገራችን ከወያኔ አስተዳደር ባሻገር በጭላንጭል የሚታየውን መልካም አስተዳደር እንዲሰፍን፤ ታሪካዊ "የዲሞክራሲ ሽግግር" ለውጥ ማለትም ቅይጥና ፕሬዝዳንታዊ አስተዳደር እንደ አማራጭ መቅረብ ይኖርበታል። አገራችን የተሻለ ጊዜ መጥቶላት ለማየት የሁላችንም ምኞት ነው። ህገ መንግስት መረቀቅም ሆነ መፅደቅ ያለበት በአገሪቷ ነዋሪዎች ነው እንጂ በፓርቲ መሪዎች ወይም ስልጣን ላይ ባሉ ግለሰቦች ችሮት ሊሆን አይገባውም። ኢትዮጵያ ውስጥ ሰላምና መልካም አስተዳደር ቢሰፍን እንዲሁም ጠንካራ የዲሞክራሲ ስርዓት ቢዳብር ጎረቤት አገራትም ከዚህ ከፍተኛ ጥቅም እንደሚያገኙ የታወቀ ነውና። እኔ በጭላንጭል የማያት የወደፊቷ ኢትዮጵያ ይህችን ትመስላለች።

* የዚህ መጣጥፍ አቅራቢ በዓለም አቀፍ የግል ኩባንያዎች ውስጥ በፋይናንስ ዘርፍ እየሰራ ይገኛል። በምጣኔ ሃብትም ዶክትሬት አለው።

አስተያየት ካሎት፤ TAYELE@YAHOO.COM ሊያገኙኝ ይችላሉ። @ Nov 2015

አስጀምሮ ላስጨረሰኝ አምላክ ምስጋና ይድረሰው።

ዋቢ ሰነዶች

[1] ESAT Special program On Ethiopia and Horn of Africa Conference፡ https://www.youtube.com/watch?v=StmaU-W6DoA&feature=player_embedded
[2] መፅሐፍ ቅዱስ ኦሪት ዘጸአት 2፡15
[3] www.Ethiopianorthodox.org - የኢትዮጵያውያን አባቶች ታሪክ
[4] Encarta world English dictionary, St Martin's Press NY page 773
[5] Black's Law Dictionary, West Publishing Co. 1981 Pg 695-697
[6] Martin Luther, Library edition. Published by arrangement with Upper Publications, LLC and Viking Penguin, 2004
[7] American Spectrum, encyclopedia 1991 page 446
[8] የቀዳማዊ ኃይለሥላሴ መንግሥት፤ ዘውዴ ረታ፤ Laxmi Publications LTD 2012 ምዕራፍ ፪ ገጽ 18
[9] Mafia - an organized international body of criminals, operating originally in Sicily - having a complex and ruthless behavioral code. - any organized group using extortion and other criminal methods.- a closed group of people in a particular field, having a controlling influence.
[10] Gabor Toka: Hungary
[11] www.wikipedia.com - Hungary
[12] http://countrymeter.info/en/ethiopia/economy
[13] In Hungary, there are 13 recognized minorities including Germans, Slovaks, Croats, Romanians, Poles, Bulgarians, Greeks, Armenians, Ruthenians, Serbs, Slovenes and Ukrainians. Roma represent the largest minority population, generally estimated between 200,000 and 600,000
[14] ANDRÁS BOZÓKI ፡THE ROUNDTABLE TALKS OF 1989
[15] http://www.ethiomedia.com/15store/ethiopian_economy_under_tplf.pdf
[16] መስፍን ወ/ማርያም - ኢትዮጵያ ከየት ወዴት
[17] http://www.BBC.com/news/world-africa-33861620
[18] ጉግሣ መጽሔት ቅፅ 3፤ ቁጥር 3፤ መጋቢት 1994 ገጽ 28